ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሑፍ የአማርኛ ቋንቋ

ትምህርት ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር


# ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ተነሳሽነት ለማዳበር ያለው ሚና (አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ በፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)


በውቤ ዲሪርሳ



መስከረም/2017 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሑፍ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

**ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ተነሳሽነት ለማዳበር ያለው ሚና ((አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ በፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)**

**በውቤ ዲሪርሳ**

**ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት**

**የጥናቱ አማካሪ ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)**

**ረዳት አማካሪ ማንያለው አባተ (ዶ/ር)**

**መስከረም/2017 ዓ.ም**

**ጅማ፣ ኢትዮጵያ**

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# የሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

# የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሑፍ የአማርኛ ቋንቋ

# ትምህርት ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

«ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለው ሚና (አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ በፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት) » በሚል ርዕስ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት በውቤ ዲሪርሳ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

## የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ_________________________ ፊርማ_____________ ቀን________________

የውስጥ ፈታኝ___________________ ፊርማ_____________ ቀን________________

የውጭ ፈታኝ____________________ ፊርማ_____________ ቀን_______________

# ማረጋገጫ

«ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለው ሚና (አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ በፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)» በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሑፍ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና ጅማ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም______________________________

ፊርማ____________________________

ቀን______________________________

# ምስጋና

**ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንክ ሀሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አውቃለሁ፤ እዮብ 42÷2**

ይህን ጥናታዊ ፁሁፍ ከርሱ ጀምሮ ባሉ ሂደቶች ሁሉ ጥልቅ እውቀታቸውን በመጠቀም አስተያየትና ጥቆማ በመስጠት ለፍፃሜ እንዲደርስ ለረዱኝ አማካሪዬ ለማ ንጋቱ (ዶ/ር ) እና ማንያለው አባተ (ዶ/ር) ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ:: የትዕግስትና የጥንካሬ ባለቤት የሆነቺኝ እናቴ ወ/ሮ ሸዋዬ ደበሬ እስከ ፍፃሜዬ ባትሆኝም እግዚአብሔር አምላክ ነብስሽን በገነት ያኑርልኝ እላለሁ:: ጥናቱን በምሰራበት ወቅት በሞራል በሃሳብ ያልተለየኝ ባለቤቴ እስራኤል መለሰ እንዲውሁም ውድ ልጄ ማክቤል እስራኤል በኮምፒዩተር እርዳታ ፈተና በመፈተን በተለያዩ ቁሶች የተራዱኝ ወንድም ፋሲካ አክሎክ፣ መ/ር ዘመድአገኝ ዘውዴ፣ ፈይሰል ራያ ፣ካሳሁን ተካ፣ ክንፈ ሃይለማርያም፣ እንዲሁም በማናቸውም መልኩ እገዛ ላደረጉልኝ በሙሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

# የይዘት ማውጫ


ማረጋገጫ ........ ii

ምስጋና ........ iii

የይዘት ማውጫ ........ iv

የሠንጠረዥ ማውጫ ........ vii

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3. የጥናቱ ጥያቄዎች ........ 4

1.4. የጥናቱ ዓላማ ........ 5

1.5. የጥናቱ መላምት ........ 5

1.6. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 6

1.7. የጥናቱ ወሰን ........ 6

1.8. የጥናቱ ውስንነት ........ 7

1.9. የቁልፍ ቃላት ፍቺ ........ 7

ምዕራፍ ሁለት ........ 8

ክለሳ ድርሳናት ........ 8

2.1. የማንበብ ክሒል ምንነት ........ 8

2.2. የአንብቦ መረዳት ምንነት ........ 9

2.3. ላይ-ታች የማንበብ ሞዴል (Top-Down Reading Model) ........ 11

2.4. የማንበብ ተነሳሽነት ........ 12

2.5. የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተዛምዶ ..................... 15

2.6. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..................... 17

ምዕራፍ ሶስት ..................... 21

የአጠናን ዘዴ ..................... 21

3.1. የጥናቱ ዘዴ ..................... 21

3.2. የጥናቱ አካላይ ..................... 21

3.3. የናሙናዎች አመራረጥ ..................... 22

3.3.1. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ ..................... 22

3.3.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ ..................... 22

3.3.3. የተጠኚዎች አመራረጥ ..................... 22

3.3.4. የማስተማሪያ ምንባቦች አመራረጥ ..................... 23

3.4. የመማር ማስተማር ሒደት ..................... 24

3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ..................... 25

3.5.1. ፈተናዎች ..................... 25

3.5.2. የጽሑፍ መጠይቅ ..................... 27

3.6. የመረጃ አተናተን ..................... 28

ምዕራፍ አራት ..................... 29

የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ..................... 29

4.1. የመረጃ ትንተና ..................... 29

4.1.1. ከቅድመ ፈተናው የተገኙት መረጃዎች ትንተና ..................... 29

4.1.2. ከቅድመ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..................... 31

4.1.3. ከድህረ ፈተናው የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..................... 33

4.1.4. ከድህረ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..................... 34

4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 37
ምዕራፍ አምስት ........ 43
የጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ እና አስተያየት ........ 43
5.1. የጥናቱ ማጠቃለያ ........ 43
5.2. የጥናቱ መደምደሚያ ........ 45
5.3. የጥናቱ አስተያየት ........ 47
ዋቢ ጽሑፎች ........ 49
አባሪዎች ........ 53
አባሪ አንድ፤ የቅድመ ትምህርት ፈተና ........ 53
አባሪ ሁለት፤ የድህረ ትምህርት ፈተና ........ 58
አባሪ ሶስት፤ የማንበብ ተነሳሽነት ለመለካት የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ........ 63
አባሪ አራት፤ የፈተናዎች ውጤት ........ 65
4.1. የቅድመ ፈተና ውጤት ........ 65
4.2. የድህረ ፈተና ውጤት ........ 67
አባሪ አምስት፤ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ........ 69
5.1. የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ........ 69
5.2. የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ........ 71
5.3. የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ ........ 73
5.4. ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ቁጥጥር ቡድን ........ 75

# የሠንጠረዥ ማውጫ

**ሠንጠረዥ** **ገጽ**

ሠንጠረዥ 1፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና...........29

ሠንጠረዥ 2፡- የቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና.....31

ሠንጠረዥ 3፡- የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና.............33

ሠንጠረዥ 4፡- የድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት...35

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካትም ሁለት የ10ኛ ክፍል ምድቦችን በእጣ በመምረጥ ከፊል ሙከራዊ ጥናት የተከናወነ ሲሆን ለጥናቱ ያገለገሉት መረጃዎችም በፈተናና በጽሑፍ መጠይቅ ተሰብስበው በባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁን መረጃዎችም ሆነ የፈተና መረጃዎች ትንተና እንዳመለከቱት ከጥናቱ ትምህርት በፊት የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ተመጣጣኝ ነው (የቅድመ ፈተና ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት፡- $P=0.072>0.05$፤ የቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት፡- $P=0.566>0.05$)፡፡ ይህንን ተከትሎም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ላይ ታች የንባብ ሞዴልን በመጠቀም፣ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ ዘወትራዊውን የንባብ ትምህርት ሂደት በመጠቀም ለ5 ሳምንታት (ለ10 ክፍለ ጊዜዎች) የንባብ ትምህርትን ተምረዋል፡፡ ትምህርቱ ተሰጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ከቅድመ ፈተናው ጋር ተመሳሳይ የሆነ ድህረ ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል፤ የጽሑፍ መጠይቅም ሞልተዋል፡፡ ከፈተናውና ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኙትን መረጃዎች በመውሰድም የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች መሰረት ያደረገ የመረጃ ትንተና ተከናውኗል፡፡ የመረጃ ትንተናዎቹ እንደሚያመለክቱት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የድህረ ፈተና አማካይ ውጤትና የድህረ ትምህርት ጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በጉልህ ይበልጣል (የድህረ ትምህርት ፈተና ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት፡- $P=0.001<0.05$፤ የድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት፡- $P=0.000<0.05$)፡፡ ከዚህ ውጤት በመነሳትም ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው ተደምድሟል፡፡ በዚህም መነሻነት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ታች የንባብ ሞዴልን አጽንዖት ሰጥተው እንዲጠቀሙ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አሰልጣኞች መምህራንን ሲያሰለጥኑ እጩ መምህራኑ ሞዴሉን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እንዲያደርጉ፣ የማስተማሪያና መማሪያ ቁሳቁስ አዘጋጁት ላይ ታች ሞዴል አተገባበርን የተመለከተ ገለጻ በቁሳቁሶቹ እንዲያካትቱና ሌሎች አጥኚዎች ተጨማሪ ጥናቶችን እንዲያደርጉ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጅ ኑሮውን ለማሻሻል በርካታ ተግባራትን ያከናውናል፡፡ ከተግባራቱ መካከልም በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተጻፉ ጽሑፎችን ማንበብ፣ አንብቦም መልእክቱን መረዳት ይገኝበታል፡፡ የዘርፉ ምሁራን እንደሚያስረዱት ማንበብ በቦታ ርቀት ስለማይገደብ ሕይወትን ለማሻሻል ግንባር ቀደሙን ቦታ ይይዛል፡፡ በዚህም ምክንያት ሰዎች በእውቀት ልቀው በመገኘት ሕይወታቸውን ለማሻሻል ከማንበብ ተግባር መራቅ እንደሌለባቸው ይታመናል፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የማንበብ ክሒልን ማካተት ያስፈለገውም ይህንን ጉዳይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

ማንበብ ለሰው ልጆች አእምሮ መጎልበትና ለተማሪዎች የትምህርት ስኬት እጅግ በጣም አስፈላጊ ክሒል እንደሆነ Cunningham (1998) ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም ግን አንባቢ ያነበበው ጽሑፍ የያዘውን ሀሰብ በሚገባ መገንዘብ ካልቻለ የማንበብ ተግባሩ ቃላትን ከማነብነብ የዘለለ ጠቀሜታ እንደሌለው ምሁሩ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Underwood (1994) እንደሚገልጹት ተማሪዎች ሊያዳብሯቸው ከሚገቡ በጣም አስፈላጊ ክሒሎች ውስጥ የአንብቦ መረዳት ክሒል ግንባር ቀደሙ ክሒል ነው፡፡

Meiryun (1995) እንደገለጹት ማንበብ ከተጻፈ ነገር መረጃ የመውሰድና ትርጉሙንም የመረዳት ሂደት ነው፡፡ በተጨማሪም ማንበብ ከተጻፈ ነገር ማገናዘብን፣ ማደራጀትን፣ መረዳትን፣ ማስታወስን፣ ምክንያታዊነትን፣ መገምገምን፣ ማሰብን፣ ማስተዋልን፣ ወዘተ የሚጠይቅ ክሒል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ውጤታማ አንብቦ የመረዳት ችሎታ የጽሑፍን መልዕክት ከመረዳት አልፎ የጸሀፊውን ስሜት፣ አተያይና ዝንባሌ ለመገምገም ጥረት ያደረጋል፡፡ እንዲሁም ውጤታማ የአንብቦ መረዳት የመማር ልምዶችና ጥልቅ አስተሳሰብን ያቀናጀ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህም ምክንያት እንደ Harmer (1991) እና Ur (1996) ያሉ የዘርፉ ምሁራን ማንበብ በጽሁፍ የሰፈረን ሀሳብ መርምሮ መልዕክቱን ለመረዳት ወይም ለመገንዘብ የሚያስችል የመቀበያ ክሂል እንደሆነ ያሳስባሉ፡፡

የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማሳደግ በርካታ ተግባራትን ማከናወንን እንደሚጠይቅ የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ Meiryun (1995) እንደሚገልጹት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር የተለያዩ እውናዊ ዓውዶችን መፍጠር፣ ከማስተማሪያ ስልቶች ውስጥም መምህራን ተማሪዎች አቀላጥፈው እንዲያነቡ ማገዝ፣ የምንባቡን መልዕክት አንብበው እንዲረዱ ማድረግ፣ የተለያዩ መጽሔቶችንና ጆርናሎችን ከቤተ መጻሕፍት ገብተው እንዲያነቡ መገፋፋትና ማበረታታት፣ የቃላት ዕውቀታቸውን እንዲያሻሽሉ መዝገበ ቃላትን እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ በክፍል ውስጥ የተለያዩ አጫጭር ምንባቦችን በማቅረብ ተማሪዎች ልምምድ እዲያደርጉ፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የሚማሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ Underwood (1994) እንደሚገልፁት ብዙዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቃላትን በትክክል የማንበብ ችግር ባይታይባቸውም ያነበቡት ጽሑፍ የያዘውን ሀሳብ የመረዳት ችግር በስፋት ይስተዋልባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ Konlly (1992) ተማሪዎች በሚኖራቸው የትምህርት ቤት ቆይታ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ተፈላጊው የችሎታ ደረጃ ላይ እንደማይደርስ ይገልፃሉ፡፡

የዘርፉ ምሁራን እንደሚገልጹት የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተለያዩ ምክንያቶች ዝቅ ሊል ይችላል፡፡ Ellis (2004) እንደሚገልጹት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት ጉዳዮች ሰባት ናቸው፡፡ እነሱም የቋንቋ አመለካከት፣ የመማር ስልት፣ ተነሳሽነት፣ ጭንቀት፣ ስብዕና፣ የተማሪዎች እምነት እና የመማር ዘዴ ናቸው፡፡ Dornyei (2005) በበኩላቸው እንደ ተነሳሽነት፣ አመለካከት፣ ችሎታ፣ ወዘተ የመሳሰሉትን በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም Westwood (2008) የአንብቦ መረዳት ችሎታ በተለያዩ ምክንያቶች ዝቅተኛ ሊሆን መቻሉን ገልጸው የንባብ ሞዴሎችን በአግባቡ ተጠቅሞ አለማንበብ አንዱና ዋናው ምክንያት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት የምሁራን ሀሳብ እንደሚያመለክተው ብዙ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከሚጠበቀው በታች ነው፡፡ ይህም በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከምክንያቶቹ ውስጥ ተገቢ ያልሆነ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም፣ የማንበብ ተነሳሽነት አለመኖር፣ ተገቢ ያልሆኑ የንባብ ሞዴሎችን ተጠቅሞ ማንበብ እና ለንባብ በጎ አመለካከት አለመኖር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን እንቅፋቶች ማስወገድ ወይም ተጽዕኖቻቸውን መቀነስ ከተቻለ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር ይቻላል ማለት ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም ለአንብቦ መረዳት ችሎታ አለመዳበር አንዱ እንቅፋት የሆነው የንባብ ሞዴል ተመርምሯል፡፡ በዚህም የላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለው አስተዋጽዖ ተመርምሯል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከሚጠበቀው በታች እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ እንዲሁም አጥኝዋ በነበራት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህርነት ልምድ ይሄንኑ ማረጋገጥ ችላለች፡፡ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ከ1980ዎቹ ጀምሮ በርካታ ጥናቶች ተከናውነዋል፤ በመከናወን ላይም ናቸው፡፡ በየጊዜው የተደረጉት ጥናቶች በሙሉ የሚያመለክቱት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከሚጠበቀው በታች መሆኑን ነው፡፡ ከ2000 ዓ.ም በኋላ የተሰሩት ጥናቶችም ቢሆኑ የሚያመለክቱት ተመሳሳይ ውጤት ነው፡፡

የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ሊሆን የቻለው በተለያዩ ምክንያቶች እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ተላውጦዎች ውስጥ የማስተማሪያ ምንባቦች የተነባቢነት ችግር፣ የመምህራን የትምህርት አቀራረብ ችግር፣ የንባብ ሞዴሎች አጠቃቀም ችግር፣ የማንበብ ተነሳሽነት ችግር፣ ወዘተ. የመሳሰሉት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከእነዚህ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ተላውጦዎች ውስጥ የንባብ ሞዴል አጠቃቀም ችግር እና የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ችግር ጥናት ተደርጎባቸው መፍትሄ ቢሰጣቸው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ ጉልህ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው አጥኚዋ ማመኗ ተቀዳሚው አነሳሽ ምክንያቷ ነው፡፡

ሌላው አጥኝዋ በዚህ ርዕስ ላይ ጥናት እንድታደርግ ያነሳሳት ጉዳይ ቀደም ሲል ከተከናወኑ ጥናቶች የተገኙት ውጤቶች መለያየት ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜዎች ላይ ታች የንባብ ሞዴሎች ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው አስተዋጽዖ ምን ያህል እንደሆነ የመረመሩ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከጥናቶቹ የተገኙት ውጤቶች ወጥነት አይስተዋልባቸውም፡፡ እንግዳ (1992) ያደረጉት ጥናት እንደሚያመለክተው ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ግሩም (2003) እና አንድነት (2010) ባከናወኑት ጥናት የተገኘው ውጤት ታች ላይ የንባብ ሞዴል ከላይ ታች የንባብ ሞዴል የበለጠ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር እንደሚጠቅም ያመለክታል፡፡ ይህም የጥናቶቹ ውጤት ወጥ አለመሆኑን ያመለክታል፡፡ በጥናቶቹ ከተገኙት ውጤቶች ውስጥ ትክክለኛው የትኛው እንደሆነ ለማረጋገጥ አጥኝዋ መፈለጓም ሌላኛው አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፡፡ ጥያቄዎቹም ለጥናቱ በመሪነት ያገለገሉ ሲሆን ቀጥሎ የቀረቡት ናቸው፡፡

- ✓ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ አስተዋጽዖ ይኖረው ይሆን?
- ✓ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ አስተዋጽዖ አለው?
- ✓ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በቅድመ ፈተና እና ድህረ ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለ?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ ላይ ታች  የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ በንኡስነት ደግሞ የሚከተሉት ሶስት ዓላማዎች ተሳክተዋል፡፡

- ✓ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር፤
- ✓ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ መርዳት አለመርዳቱን ማረጋገጥ፤
- ✓ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በቅድመ ፈተና እና ድህረ ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖርም ማረጋገጥ፡፡

## 1.5. የጥናቱ መላምት

በዚህ ጥናት ከላይ የቀረቡት ዓላማዎች ይሳኩ ዘንድ የሚከተሉት መላምቶች ተሰንዝረዋል፡፡

- ✓ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ የለውም፤
- ✓ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ አለው፤
- ✓ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ የለውም፤
- ✓ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ አለው፤

## 1.6. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ተከናውኖ ሲጠናቀቅ ከሚገኘው ውጤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ተማሪዎችና አጥኚዎች ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በቅድሚያ ከዚህ ጥናት የሚጠቀሙት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ በጥናቱ ዓላማ እንደተገለጸው በጥናቱ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ የጥናቱን ውጤት በመመርኮዝም ለመምህራን አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ በተሰጠው አስተያየት መሰረትም መምህራን ላይ ታች የንባብ ሞዴልን የትምህርቱን ዓላማ መሰረት ባደረገ መልኩ እንደሚጠቀሙበት ይታመናል፡፡ ይህም የተማሪዎቻቸውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በማዳበር ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል፡፡

በመጨረሻም ይህ ጥናት መከናወኑ ለሌሎች አጥኚዎች ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ዓውዶችን በመቀያየር ተደጋጋሚ ጥናቶችን ማከናወን ተገቢ ነው፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግም ሌሎች አጥኚዎች በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ጥናት ሊያካሂዱ እንደሚችሉ ይታሰባል፡፡ በዚህ አጋጣሚም የዚህን ጥናት ውጤት በመነሻ ሀሳብነት ሊወስዱት ይችላሉ፤ በተጨማሪም የጥናቱን ውጤት በመረጃ ምንጭነት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ ይህም የሚያመለክተው ይህ ጥናት ለአጥኝዎች አስፈላጊያቸው መሆኑን ነው፡፡

## 1.7. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተከናወነው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት፣ በጅማ ዞን፣ ጉማ ወረዳ በሚገኘው ሊሙ ሻይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በዚህ ትምህርት ቤት ላይ ብቻ የተገደበ ሲሆን በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን አላካለለም፡፡ በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ ተማሪዎች ውስጥ በ2015 ዓ.ም በ10ኛ ክፍል የሚማሩ ሲሆኑ ሌሎች የክፍል ደረጃዎች በጥናቱ አልተካተቱም፡፡ምክንያቱም አፋቸውን በአፍን ኦሮሞ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመጨረሻቸው ስለሆነ ቅድሚያ ለእነሱ ለመስጠት ሲባል ሌሎችን አላካተተም። ጥናቱ ያተኮረባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በተመለከተ ይህ ጥናት በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ፣ በተማሪዎች

የማንበብ ተነሳሽነትና በላይ ታች የንባብ ሞዴል ላይ ብቻ የተገደበ ነው፤ በመሆኑም ከእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ውጭ ያሉ ማንኛቸውም ጉዳዮች በዚህ ጥናት አልተካተቱም፡፡

## 1.8. የጥናቱ ውስንነት

ከላይ በጥናቱ ወሰን እንደተገለጸው ይህ ጥናት የሚከናወነው በአንድ ከተማ ላይ በሚገኝ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የወካይነት ችግር ሊኖርበት ይችላል፡፡ ማለትም ተጠኚዎቹ ናሙናዎች ከአንድ ትምህርት ቤት ብቻ የተመረጡ ናቸው፡፡ ይህ መሆኑም በሌሎች የመኖሪያ ዓውድ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች በጥናቱ ባለመካተታቸው የጥናቱ ውጤት ላይወክላቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ጥናቱ ውስንነት ሊኖርበት እንደሚችል ይታሰባል፡፡

## 1.9. የቁልፍ ቃላት ፍቺ

ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት የያዟቸው ፍቺዎች እንደዓውዳቸውና አገባባቸው የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጥናት የያዟቸው ፍቺዎችም የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

- **አንብቦ የመረዳት ችሎታ፡-** አንድን ምንባብ ያለማንም እገዛ በማንበብ ምንባቡ የያዘውን ሀሳብ የመገንዘብና ምንባቡን በተመለከተ ለሚጠየቁት ጥያቄዎች መልስ የመስጠት ችሎታን ይመለከታል፡፡

- **የንባብ ተነሳሽነት፡-** ተማሪዎች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ የተጻፈን ጽሑፍ (ምንባብ) ለማንበብ ያላቸውን ፍላጎት ያመለክታል፡፡

- **ላይ ታች የንባብ ሞዴል፡-** አንድን ምንባብ በማንበብ ሀሳቡን ለመረዳት በምንባቡ ብቻ ባለመገደብና የቀደመ እውቀትም በመጠቀም የማንበብ ሂደትን ይመለከታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር የተገናኙ ድርሳናት ይፈተሻሉ፡፡ በዚህም መሰረት የጥናቱን ርእሰ ጉዳዮች የሚመለከቱት የማንበብ ክሂል፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ፣ የማንበብ ተነሳሽነት፣ ወዘተ. የመሳሳሉትን የተመለከቱ ንድፈ ሀሳባዊ ትወራዎች የዘርፉ ምሁራንን ሀሳብ በማጣቀስ ይቀርባሉ፤ ከጥናቱ ጋር ዝምድና ያላቸው ጥናቶችም ተዳስሰው ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው አንድነት ልዩነቶች ይብራራሉ፡፡

## 2.1. የማንበብ ክሒል ምንነት

የማንበብ ክሒል ምንነትን በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን የየራሳቸውን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ የምሁራኑ ብያኔ መመሳሰል የሚስተዋልበት ሲሆን ይኸውም በጽሑፍ የቀረበን ሀሳብ ማዕከላዊ መልእክት ለመረዳት የሚደረግ ጥረት እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡ የማንበብ ሒደቱም የተለያዩ ተግባራት ይከናወንበታል፡፡

Williams (1984: 3) የማንበብ ክሒልን እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡ ‹‹ማንበብ የተገለጸውን መረጃ የማግኘትና የመረዳት ሒደት ነው፡፡ የመረዳቱ ሁኔታም ጽሑፉ እንደሚነበብበት ዓላማ የማንበቢያ ስልቱም የተለያየ ሊሆን ይችላል››፡፡ Grellet (1981: 3) እንደሚነበብበት ዓላማ የአነባበብ ስልቱም የተለያየ መሆኑን ገልጸው ስልቶቹንም ‹‹...ከማስታወቂያ ላይ አንድን ፍሬ ሃሳብ ለማግኘት በገረፍታ የሚነበብ ሲሆን ሳይንሳዊ ምርምርን የመሳሰሉ ጽሑፎችን ደግሞ በጥልቀት ማንበብን ይጠይቃል›› በማለት አስረድተዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተገናኘ Wallace (1992) እንደሚገልጹት የማንበብ ተግባር አንባቢው ከጸሐፊው ጋር ግንኙነት ለመፍጠርና የተጻፈውን ሀሳብ ለመረዳት፣ ተረድቶም ትርጉም ለመስጠት የሚደረግ ግላዊ ጥረት ነው፡፡ ይህ ሀሳብ እንደሚያሳየው አንድ ግለሰብ አንድን

ጽሑፍ በሚያነብበት ወቅት የጸሐፊውን መልእክት ለመረዳት ጥረት ያደርጋል፤ ተረድቶም ለሀሳቡ ትርጉም በመስጠት የመልእክቱን ትክክለኛነት ወይም ስህተትነት ያረጋግጣል፡፡

ከላይ የቀረቡት ምሁራን ሀሳብ እንደሚያሳየው ማንበብ በአንድ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ፊደላትን፣ ቃላትን፣ ሐረጋትን፣ ዓረፍተ ነገሮችን፣ ወዘተ. የመጥራት ተግባር ብቻ አይደለም፡፡ ይህንን ማድረግ ብቻውን ፊደላትን ከማነብነብ የዘለለ ፋይዳ የለውም፡፡ ማንበብ የሚባለው አንድን ጽሑፍ በማንበብ፣ በመመርመር፣ በመገንዘብ፣ በመረዳትና በመገምገም ከጸሐፊው ሐሳብ ጋር ግንኙነት የሚደረግበት ተግባር ነው፡፡ በግምገማ ሒደቱም ከጽሑፉ ያገኛቸውን ማስረጃዎች መሰረት አድርጎ በሀሳቡ ይስማማል፤ ወይም ሀሳቡን ይነቅፋል፡፡

## 2.2. የአንብቦ መረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳትን በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን የየራሳቸውን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ምሁራኑ እንደሚያስረዱት አንብቦ መረዳት ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ምንባቦች በጥልቀት በማንበብ መልእክቱን መርምረው የሚያወጡበት የማንበብ ክሒል ውጤት ነው፡፡ እንደ Wallace (1992) ማብራሪያ አንብቦ መረዳት በጥልቀት ማሰብን የሚጠይቅና አንድን ምንባብ በማንበብ ሀሳቡን መገንዘብ፣ ጽሑፉን በራስ ተርጉሞ መረዳት፣ መተንተንና መገምገም የመሳሰሉትን ችሎታዎች የሚጠይቅ የማንበብ ትምህርት አንዱ አላባ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው አንብቦ መረዳት የማንበብ ትምህርት አንዱ ግብ መሆኑን ነው፡፡

Wallace (1992) እንደገለጸው አንብቦ መረዳት አንባቢ ከአንድ ምንባብ ትርጉም የሚያወጣበት ተራክቧዊ ሂደት ነው፡፡ አያይዞም ሁለት የመረዳት ክሒሎች እንዳሉና እነሱም ቀጥተኛ እና አንድምታዊ እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ ቀጥተኛ መረዳት የሚባለው በምንባቡ በቀጥታ የተገለጸን ሀሳብ ማወቅ ሲሆን ሀቅን የማስታወስ ወይም መሰረታዊ ግንዛቤ የማግኘት ችሎታ የማይጠይቅ ቀላል ክሒል ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ አንድምታዊ መረዳት የሚያመለክተው በጽሑፉ ከተባለው ነገር በመነሳት በግልጽ ያልቀረበን ሀሳብ ማውጣት ሲሆን ይህንን ለማድረግ ጥልቅ የቋንቋ እውቀት ያስፈልጋል፡፡

በተመሳሳይ መንገድ Smith (1985)ም ለአንብቦ መረዳት የራሳቸውን ገለጻ ይሰጣሉ፡፡ የምሁሩ ገለጻ እንደሚያመለክተው አንብቦ መረዳት አንድ አንባቢ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ የማግኘት ተግባር ነው፡፡ ምሁሩ እንዳብራሩት አንባቢ አንድን ምንባብ ሲያነብ በውስጡ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ያገኛል፡፡ መልስ ለማግኘት በሚያደርገው የማንበብ ሂደትም ዓላማውን ያሳካል፡፡ በመሆኑም አንባቢ ለነበረበት ጥያቄ ከማንበብ ተግባሩ መልስ ማግኘት ካልቻለ አንብቦ መረዳት አልተፈጸመም ማለት ይቻላል፡፡ ይህም የሚያለክተው በአንባቢና በምንባቡ መካከል ተግባቦት ካልተፈጠረ አንብቦ መረዳት እንደማይኖር ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ Nuttal (1982) አጠናክረው ይገልጻሉ፡፡ Nuttal እንደሚሉት ማንበብ ያለመረዳት ዋጋ የለውም፡፡

Grellet (1981)ም በበኩላቸው ለአንብቦ መረዳት የራሳቸውን ገለጻ የሰጡ ሲሆን ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ምሁሩ እንደገለጹት አንብቦ መረዳት መቻል ማለት ከአንድ አሀድ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ በብቃት ማሰባሰብ መቻል ማለት ነው፡፡ በዚህ አይነት ሂደት ወስጥ አንባቢው የማይፈልገውን መረጃ እያንጓለለ በመተው የሚፈልገውን ብቻ ሊመርጥ ይችላል፡፡ ከዚህም ውጭ የአንዱን አሀድ መሰረታዊ ሃሳብ ከመረዳትም ባሻገር ዝርዝሩን በብቃት የመገንዘብ ሂደትም በዚሁ ይጠቃለላል፡፡

በአጠቃላይ አንብቦ መረዳት የጽሑፉን ይዘትና ዋናውን ሀሳብ ጨምቆ ማውጣት የሚያስችል የቋንቋ ችሎታን መመዘኛ ሂደት ነው፡፡ RAND የንባብ ጥናት ቡድን (2002) እንደሚገልጸው አንብቦ መረዳት የጽሑፍን ይዘት መረዳትን እና በተመሳሳይ ፍቻቸውን ጨምቆ የማውጣት ተግባር ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንባቢው በግልጽ በጽሑፉ ውስጥ የሌለ ማጣቀሻና ተገቢ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል፡፡ በመሆኑም አንብቦ መረዳት አንድ አንባቢ ከሚያነበው ጽሑፍ ቃሉን ወይም ጽንሰ ሃሳቡን በምንባቡ ውስጥ ካለው ውጪ ፍችውን ወይም ትርጉሙን የመፈለግ ወይም ለይቶ የማውጣት ሂደት ነው፡፡

## 2.3. ላይ-ታች የማንበብ ሞዴል (Top-Down Reading Model)

ላይ ታች የንባብ ሞዴል ከታች ላይ ሞዴል በተቃራኒ የሚተገበር ሞዴል ነው፡፡ በዚህ ሞዴል የሚያነቡ አንባቢዎች የምንባቡን ሀሳብ ለመገመት የቀደመ እውቀታቸውን መጠቀም የግድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ Anderson Et. al (1985) እንደሚገልጹት የላይ-ታች የማንበብ ሞዴል እንደ ግምት፣ ትንታኔ፣ ከጽሑፉ ውስጥ ጣልቃ በመግባት ማጠቃለልን ያካትታል። ይህም የሚያመለክተው ሞዴሉ የማንበብ ግንዛቤ (cognitive) እይታ መሆኑን ነው።

እነAnderson እነደገለጹት ይህ ሞዴል ከምንባቡ ላይ ትርጉም ለማግኘት ቃል በቃል ከመተርጎም ይልቅ የምንባቡን ዋና ዋና ሃሳቦች በመረዳት ላይ ያተኩራል። በዚህ ጊዜ ተማሪዎች እያንዳንዱን ቃል ላይረዱ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን የጽሑፉን ትርጉም (መልእክት) የመረዳት እድላቸው ሰፊ ነው። እነAnderson እንደሚያብራሩት አንድ ምንባብ በውስጡ አዳዲስ ቃላት ወይም መዋቅሮችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን አንባቢው በምንባቡ ርዕስ የቀደመ እውቀት ካለው እሱን በመጠቀም የምንባቡ አንቀጾች የያዙትን ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ምንባብን ከማንበባቸው በፊት የቀደመ እውቀት እንዲኖራቸውና ያላቸውን እውቀትም ምንባቡን ለመረዳት እንዲጠቀሙበት ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ምሁራን እንደሚያሳስቡት ላይ ታች የማንበብ ሞዴል አንባቢዎች ያላቸውን ስነ ልቦናዊ ዝግጅት ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ሞዴል ነው፡፡ Anderson Et. al (1985) እንደገለጹት የአንባቢዎች ስነ ልቦናዊ ዝግጅት የሚያስፈልገው የቀደመ እውቀታቸውን እና ከምንባቡ እንደሚያገኙ የሚገምቱትን ሀሳብ ለማቆራኘት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ አንባቢዎች በሚያነቡት ምንባብ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት በሙሉ ማንበብ አይጠበቅባቸውም፡፡ ከዚህ ይልቅ አንባቢዎች የማንበብ ተግባራቸውን ከምንባቡ ርዕስ በመነሳት የምንባቡን ሀሳብ ከመገመት ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ በመቀጠልም ምንባቡን ከቀደመ እውቀታቸውና ከግምታቸው ጋር በማገናኘት ማንበብ ይጀምራሉ፡፡ በማንበብ ተግባራቸው ላይ እያሉ ጸሐፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳብ ይመለከታሉ፡፡ በዚህ ጊዜም ቀድመው ከገመቱት

ጋር በማቀናጀት አንዳች መልእክት ያገኛሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት በመቀናጀት የሚከናወንበት ደረጃ በመሆኑም ሂደቱን ከባድ ሊያደርግባቸው ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት አንባቢያን ምንባቡን በተመለከተ የቀደመ እውቀት ከሌላቸው አንብበው መረዳት አይችሉም፡፡

Nuttal (1982) እንደሚገልጹት አንባቢያን በዚህ ሞዴል ተጠቅመው ለማንበብ የቀደመ እውቀት ሊኖራቸውና ያንን እውቀትና ልምድ መነሻ ቢያደርጉ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ያሳድጋል፡፡ የምንባቡንም መልዕክት ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት በመተንበይና መላምቶች በማስቀመጥ በሚያነቡበት ወቅት ደግሞ እነዚህን እያረጋገጠ ከቀደመ እውቀቱ ጋር እያዛመደ መልእክቱን ለመተርጎምና ለመረዳት ጥረት የሚደረግበት ሞዴል ነው፡፡

Nunan (1993) እንደሚያብራሩት በዚህ ሞዴል የአንብቦ መረዳት ትምህርትን ለመማር ሰዋስዋዊ እውቀት ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ከሰዋስው እውቀት በተጨማሪ እውቀቱን የሚያዳብር ዳራዊ እውቀት ያስፈልጋል፡፡ አንባቢው ሰዋስዋዊ እውቀትና እውቀቱን የሚያገኝበት ዳራዊ እውቀት ሲኖረው ሞዴሉን በመጠቀም በሚገባ ማንበብ እንደሚችል ጨምረው ያስረዳሉ፡

## 2.4. የማንበብ ተነሳሽነት

Harmer (2007: 28) ተነሳሽነትን ‹‹አንድ ሰው የሆነ ነገር ለማሳካት ነገሮችን እንዲያደርግ የሚገፋው አንዳች ውስጣዊ ግፊት ተነሳሽነት ይባላል›› በማለት በይነውታል። በተጨማሪም Field (2004) ተነሳሽነት የሰውን ባህርይ የሚመራና በአእምሮ የሚያበረታታ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም በጊዜ ሂደት ተነሳሽነት ወደ ንቁነት ሊለወጥ እንደሚችል ያሳስባሉ፤ በተለይም ግብን ለማሳካት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ንቁነት የመቀየር አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡

ተነሳሽነት በአንድ ዓላማ ላይ የተመሰረተስሜት በሚታይበት ሰው ውስጥ የሚስተዋል የኃይል ለውጥ እንደሆነ Takase (2007) ያስረዳሉ፡፡ አያይዘውም ተነሳሽነት በአንድ ሰው ውስጥ የኃይል ለውጦችን በማስከተል አእምሮ ውስጥ ስሜታዊነትን፣ ምልክቶችንና ስሜቶችን ሊያሳይ፣ ብሎም አንድን ነገር ሊያከናውን እንደሚችል ያብራራሉ፡፡

ተነሳሽነት በእቅድ፣ በፍላጎትና በሚነሳ ዓላማ መልክ ሊፈጠር ይችላል፡፡ የሰው ልጅ ተነሳሽነት በተለያዩ ምክንያቶች መነሻነት ሊፈጠር እንደሚችል Harmer (2007) ያስገነዝባሉ፡፡ ከምክንያቶቹ ውስጥም ለሕይወት የሚኖር ምኞት፣ አንድን ነገር የማግኘት ምኞት፣ ስልጣን የማግኘት ፍላጎት፣ የአንድ ነገር ምስጢራዊ ምኞት እንደሚገኙበት ያስረዳሉ፡፡ በመማር እንቅስቃሴው ውስጥ ተነሳሽነት ለተማሪዎች እንደ አጠቃላይ ተማሪዎች ማነቃቂያ፣ መተማመኛና ለትምህርት እንቅስቃሴ መኖር አቅጣጫ የሚሰጥ በመሆን ያገለግላል፤ በዚህም ተማሪዎቹ በመማር ማስተማር እንቅስቃሴው ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ ምክንያት ይሆናቸዋል (Wang, 2009)፡፡

Wang (2009) እንደሚያስረዱት የተማሪዎች ተነሳሽነት የተማሪዎችን በመማር ማስተማር ሂደቱ የመሳተፍና ስኬታማ የመሆንን ፍላጎት ያመለክታል። ለመማር ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በራሳቸው ብቃት ተግባራትን ይመርጣሉ፤ ዕድሉን ሲያገኙም እርምጃ ይወስዳሉ፤ እንዲሁም የትምህርት ተግባር አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፤ በእንቅስቃሴ ላይ እንደ ብሩህ ተስፋ፣ የማወቅ ጉጉት እና ፍላጎት በአጠቃላይ አዎንታዊ ስሜቶችን ያሳያሉ። በአንጻሩ ደግሞ ብዙም ተነሳሽነት የሌላቸው ወይም ያልተነቃቁ ተማሪዎች ቀርፋፎች፣ ጠንክረው ለመስራት ፍላጎት የሌላቸውና ችግሮችን የማይጋፈጡ ይሆናሉ፡፡

የተነሳሽነት ሚና ተማሪዎች ደስተኛ እንዲሆኑና የመማር መንፈሳቸው እንዲያድግ ማድረግ ነው፡፡ ከፍተኛ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በመማር እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ኃይል ይኖራቸዋል፡፡ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ ያለው አንድ ተማሪ ተነሳሽነት ባለመኖሩ ምክንያት ስኬታማ ላይሆን ይችላል፡፡ የመማር ሂደት በተገቢው ተነሳሽነት ከታጀበ በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ ይሆናል፤ በመሆኑም የተማሪዎችን ተነሳሽነት ማሳደግ የመምህራን ኃላፊነት ነው፡፡

Guthrie & Wigfield (2000) እንደሚያስረዱት የማንበብ ተነሳሽነት ለማንበብ ክሂል ማደግ ቁልፍ ሚና አለው፡፡ አያይዘውም የተማሪዎችን ተነሳሽነት በማሳደግ ከሚገኙ በጎ ውጤቶች ውስጥ አንዱና ግንባር ቀደሙ የማንበብ ክሂል እንደሆነ ያሳስባሉ፡፡ በተጨማሪም Al‐Bargi (2015) እንደሚገልጹት ማንበብ በተለያዩ የተነሳሽነት አተገባበር ምክንያቶች የሚመጣ ክሂል ነው፡፡ ከአተገባበሮቹ መካከልም የተፈጥሮ ተነሳሽነት፣ የራስ ብቃት፣ የማህበራዊ ተነሳሽነትና ተማሪዎች ያላቸው የመፈፀም ብቃት ደረጃ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ሲጀምሩ የተነሳሽነት ደረጃቸው እየቀነሰ እንደሚሄድ ይገልፃሉ፡፡ ተነሳሽነታቸው የመቀነሱ ምክንያት ደግሞ ማንበብ አለመቻላቸውን ሲገነዘቡ እና የጓደኞቻቸው ተፅዕኖ እንደሆነ ሲገልፁ ሌላው የማንበብ ተነሳሽነት ተፅዕኖ የመማር ብልሃቶች በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ መሰረት አለማድረጋቸው ነው፡፡

የማንበብ ተነሳሽነት ችግሮችን ለመቀነስና ችግሩን ለመፍታት መምህራንና ተማሪዎች የራሳቸውን ግብ በሚያስቀምጡበት ወቅት በጋራ መግባባትና ተማሪዎችም ራሳቸውን መቆጣጠርና መምራት እንዳለባቸው Al‐Bargi (2015) ይገልጻሉ፡፡ Al‐Bargi (2015) በጥናታቸው ውጤት ተመርኩዘው እንደገለጹት በማንበብ ሞዴሎችና በማንበብ ተነሳሽነት መካከል ጥብቅ ቁርኝት አለ፡፡ በተጨማሪም የማንበብ ተነሳሽነታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች በተመሳሳይ መልኩ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውም ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው የማንበብ ሞዴሎችና አንብቦ የመረዳት ችሎታ አዎንታዊ ግንኙነት እንዳላቸውና ተነሳሽነታቸው ሲጨምር አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውም መጨመሩን፣ ሲቀንስ ደግሞ መቀነሱን ነው፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ሲል የቀረቡት ሀሳቦች እንደሚያመለክቱት ተነሳሽነት የተለያዩ ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ አንድን ተግባር ለመፈጸም የሚኖርን ውስጣዊ ፍላጎት የሚያመለክት ነው፡፡ ማለትም ተነሳሽነት አንድ ነገር ለምን እና እንዴት እደሚተገበር የሚያሳይና የባህሪ ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችል ውስጣዊ ግፊት ነው፡፡ ስኬታማ የማንበብ ክሂል ትምህርትን ለማስተማር፣ ብሎም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ የማንበብ ተነሳሽነት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ማሳደግ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለማሳደግ ይረዳል፡፡ ለዚህም

የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት የሚያሳድጉ የማንበብ ሞዴልን በመጠቀም ማስተማር ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ጥናትም ከማንበብ ሞዴሎች ውስጥ አንዱ የሆነው ላይ ታች የማንበብ ሞዴል ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተጨማሪ የማንበብ ተነሳሽነታቸውን ለማሳደግ ያለው አስተዋጽዖ ይመረመራል፡፡

## 2.5. የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተዛምዶ

Baker and Wigfield (1999) እንደሚገልጹት የማንበብ ተግባር የአንባቢን ችሎታና ተነሳሽነት ይፈልጋል፡፡ Eccles, Wigfield and Schiefele (1998) እንደሚገልጹት የማንበብ ተነሳሽነት አንባቢዎችን በማያቋርጥ የማንበብ ሂደት ውስጥ እንዲቆዩ ያደርጋል፡፡ Grabe (2009) በበኩላቸው የማንበብ ተነሳሽነት የማንበብ ክሒልን ያሳድጋል፡፡ ከፍተኛ የማንበብ ተነሳሽነት ያለው አንባቢ ብዙ መጻሕፍትን ያነባል፤ አንብቦ የመረዳት ችሎታውም ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም ‹‹ከፍተኛ የማንበብ ተነሳሽነት ያለው አንባቢ ብዙ ያነባል›› ከሚለው የGuthrie (1996) ድምዳሜ ጋር ይመሳሰላል፡፡

Wang and Guthrie (2004) ውስጣዊ ተነሳሽነትና ውጫዊ ተነሳሽነት ከማንበብ ተነሳሽነት ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ለግል ፍላጎታቸውና በሌሎች ሰዎች ግፊት ሊያነቡ ስለሚችሉ ውስጣዊ ተነሳሽነት በከፍተኛ ደረጃ ከውጫዊ ተነሳሽነት ጋር እንደሚገናኝ ይጠቁማሉ፡፡ Dhanapala and Hirakawa (2016) በበኩላቸው ውስጣዊ ተነሳሽነት ከውጫዊ ተነሳሽነት ጋር አዎንታዊ በሆነ መልኩ ከተገናኘ ለአንብቦ መረዳት ትልቅ አስተዋጽዖ ያበረክታል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ Komiyama (2013) እንደሚገልጹት የማንበብ ተነሳሽነትን የሚያሳድገው ውስጣዊ ተነሳሽነት ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ Sirin and Saglam (2012) ብዙውን ጊዜ የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያለው ውጫዊ ተነሳሽነት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

የስነ ልቦና ባለሙያዎች ተነሳሽነትን በተለያዩ መንገዶች በይነውታል፡፡ Williams and Burden (1997) እንደሚገልጹት ተነሳሽነት አንድን ድርጊት ለመፈጸም ንቁ በሆነ አእምሮ ወይም በሙሉ ንቃተ ህሊና ለመፈጸም የሚኖርን ጥረት የሚያበረታታ አእምሮታዊና

ስሜታዊ ቅስቀሳ ነው፡፡ Brown (2000) የተነሳሽነት ምንነትን በተመለከተ የሚከተለውን ገለጻ ይሰጣሉ፡፡

ተነሳሽነት ከባህሮታዊያን እይታ አንጻር አንድን ተግባር ለማከናወን ማጠናከሪያ ሰጥቶ ምላሽ እንዲሰጥ ከማድረግ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከአእምሮታዊያን እይታ መሰረት ተነሳሽነት የሚመነጨው ከራሱ ከግለሰቡ ነው፡፡ ይህ እይታ ከግንባታዊያን አንጻር በማህበራዊ ዓውድ እንዲሁም በግለሰቦች ምርጫ ላይ የተመሰረተ ነው (P. 160)፡፡

ከላይ ያለው ገለጻ እንደሚያመለክተው ተነሳሽነት አንድን ተግባር ለመፈጸም የሚኖር ግፊት ነው፡፡ ነገር ግን የግፊቱ መንስኤ እንደ ንድፈ ሀሳቡ አራማጆች የተለያየ ነው፡፡ በመሆኑም ባህሮታዊያን ተነሳሽነት በማበረታቻ እንደሚመጣ፣ በአእንሯዊያን ከግለሰቡ ውስጣዊ ፍላጎት እንደሚመጣ፣ እንዲሁም በግንባታዊያን ግለሰቡ ከሚኖርበት ማህበረሰብ እንደሚመጣ ያምናሉ፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ሲል የቀረቡት ሀሳቦች እንደሚያመለክቱት ተነሳሽነት የተለያዩ ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ አንድን ተግባር ለመፈጸም የሚኖርን ውስጣዊ ፍላጎት የሚያመለክት ነው፡፡ ማለትም ተነሳሽነት አንድ ነገር ለምን እና እንዴት እደሚተገበር የሚያሳይና የባህሪ ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችል ውስጣዊ ግፊት ነው፡፡ ይህም አንድ ተግባር በሚገባ እንዲፈጸም የራሱ አስተዋጽዖ የሚኖረው ሲሆን ተጽዕኖው ከሚያርፍባቸው ነገሮች ውስጥም ማንበብ አንዱ ነው፡፡

የማንበብ ተነሳሽነት አንብቦ ለመረዳት ችሎታ መዳበር ትልቅ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ባለሙያዎች ይገልጻሉ፡፡ Alexander (1988) እንደሚገልጹት ተነሳሽነት ለማንበብ ብቃትና ትክክለኛ ማንበብን ለመለማመድ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም የማንበብ ክሒልን ለመማር ፍላጎት የሌላቸውና ክሂሉን በመማር የማይደሰቱ ተማሪዎች የማንበብ መሻሻል ሂደታቸው ዘገምተኛ ነው፡፡ እንዲሁም አዎንታዊ ተነሳሽነት በማንበብ ሂደት ትኩረትንና ትብብርን ለመጨመር ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳለው ይጠቁማሉ፡፡

Grellet (1981: 8) ተነሳሽነት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ሲገልጹ ‹‹በማንበብ ተግባር ተነሳሽነት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ የማንበብ ተነሳሽነት ተፈጥሯል ማለት አንድን ምንባብ ማንበብ የምንጀምረው የተለያዩ ጥያቄዎችንና የተወሰነ መረጃን ወይም የምንፈልገውን ሀሳብ ከምንባቡ መፈለግ ጀመርን ማለት ነው፡፡ ይህ ሀሳብን ከምንባብ የማግኘት ፍላጎትም በማንበብ ሂደቱ በአንባቢና በምንባብ መካከል ያለን ቋሚ የእርስ በእርስ ግንኙነት ያጎላል›› ይላሉ፡፡ Smith (1971) በተመሳሳይ እንደሚገልጹት የአንድ ሰው ተነሳሽነት፣ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ እምነትና ስሜት ለማንበብ ክሒል ትምህርትም ሆነ ለየትኛውም ትምህርት ስኬታማነት ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ገለጻዎች እንደሚያመለክቱት የማንበብ ተነሳሽነት በማንበብ ሂደት ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው፡፡ ተማሪዎች ለማንበብ ፍላጎት ከሌላቸው ውጤታማ የማንበብ ሂደት ማከናወን አይችሉም፤ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውም ሊሻሻል አይችልም፡፡

## 2.6. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የማንበብ ሞዴሎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ ያላቸውን ሚና የፈተሹ የተለያዩ ጥናቶች ይገኛሉ፡፡ ሆኖም ግን አብዛኛዎቹ ጥናቶች አንድ አይነት ውጤቶችን አያመለክቱም፡፡ በተጨማሪም ሞዴሎቹ የተማሪዎቹን የማንበብ ተነሳሽነት በማሳደግ ረገድ ያላቸው ሚና ብዙም አልተዳሰሰም፡፡ ይህንን ጥናት ማከናወን ያስፈለገበት አንዱ ምክንያትም በዚህ ረገድ የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት ነው፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ ያላቸው ጥናቶች ተዳስሰው ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው አንድነትና ልዩነት፣ እንዲሁም በዚህ ጥናት የተሞሉት የጥናቶቹ ክፍተቶች በአጭር በአጭሩ ይዳሰሳሉ፡፡

የመጀመሪያው ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመደው ጥናት በአንድነት (2010) የተሰራው ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ ከላይ ታች እና ከታች ላይ የማንበብ ሞዴሎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የበለጠ አስተዋጽኦ ያለው የትኛው እንደሆነ መለየት ነው፡፡ ይህንን ጥናት ከግብ ለማድረስም አፈ ፈት በሆኑ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ጥናት

ተከናውኗል፡፡ ለጥናቱ ያለገሉት መጠናዊ መረጃዎችም በፈተናና በጽሑፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ላይ ታች የማንበብ ሞዴል ከታች ላይ የማንበብ ሞዴል የበለጠ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያዳብራል፡፡

የአንድነት (2010) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽዖ መመርመሩ ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ሁለቱ ጥናቶች የሚለያዩባቸው ልዩ ልዩ ጉዳዮች አሉ፡፡ የመጀመሪያው የሁለቱ ጥናቶች ልዩነት የተጠኚ ተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ መለያየት ነው፡፡ በአንድነት ጥናት ተተኳሪዎቹ ተማሪዎች አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ሲሆኑ የዚህ ጥናት ተጠኚዎች ግን አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ የፈቱ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በዚህ ጥናት ላይ ታች የንባብ ሞዴል የማንበብ ተነሳሽነትን ለማሳደግ ያላቸው ፋይዳ ተመርምሯል፤ እነዚህ ጉዳዮችም በአንድነት ጥናት አልተፈተሹም፡፡ በመሆኑም ከኢ-አፍፈት ተማሪዎችና ከማንበብ ተነሳሽነት አንጻር በአንድነት ጥናት የታዩት ክፍተቶች በዚህ ጥናት ተሞልተዋል፡፡

ሁለተኛው ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመደው ጥናት በግሩም (2003) የተሰራው ጥናት ሲሆን ርዕሱም ‹‹የታች ላይ የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሒልን ለማዳበር ያለው ውጤታማነትና ተተግባሪነት›› የሚል ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማም ታች ላይ የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው ታች ላይ የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው፡፡

የግሩም (2003) ጥናትና ይህ ጥናት የንባብ ሞዴልን በሙከራ በመፈተሽ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽዖ የሚመረምሩ መሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ይህ ጥናት በግሩም ጥናት ያልተሞከረውን ላይ ታች የንባብ ሞዴል የመረመረ ስለሆነ ከግሩም ጥናት ይለያል፡፡ እንዲሁም በግሩም ጥናት ተጠኚዎቹ ተማሪዎች አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ሲሆኑ ይህ ጥናት የተከናወነው ደግሞ አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ በፈቱ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ ጥናት

ከአንብቦ መረዳት ችሎታ በተጨማሪ የማንበብ ተነሳሽነትም ተመርምሯል፡፡ በመሆኑም በግሩም ጥናት ያልተዳሰሱት ላይ ታች የንባብ ሞዴል፣ የማንበብ ተነሳሽነት እና ኢ-አፍፊት ተማሪዎች በዚህ ጥናት ተዳስሰው በጥናቱ የታዩት ክፍተቶች ተሞልተዋል፡፡

የመጨረሻው ተዛማጅ ጥናት የእንግዳ (1992) ሲሆን የጥናቱ ርዕስም ‹‹የቶፕ ዳውን የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት፣ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት›› የሚል ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማም ላይ ታች የንባብ ሞዴል አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎችን ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካትም በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሙከራዊ ጥናት ተከናውኗል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተውም ላይ ታች የንባብ ሞዴል አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ አለው፡፡

የእንግዳ (1992) ጥናትና ይህ ጥናት የሚመሳሰሉት ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽዖ የሚመረምሩ መሆናቸው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከሁለቱ ተላውጦዎች አንጻር ሁለቱ ጥናቶች ቢመሳሰሉም የሚለያዩባቸው ተላውጦዎችም አሏቸው፡፡ የመጀመሪያው ልዩነታቸው ይህ ጥናት ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ የፈተሸ መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም የእንግዳ ጥናት የተከናወነው አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ በፈቱ ተማሪዎች ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ በፈቱ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በእንግዳ (1992) ያልተካተቱት አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ የፈቱ ተማሪዎች እና የማንበብ ተነሳሽነት በዚህ ጥናት ተመርምረው የእንግዳ ጥናት ክፍተት ተሞልቷል፡፡

ከላይ የተቃኙት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ አላቸው፡፡ ከሶስቱ ጥናቶች ውስጥ ሁለቱ አንድ አይት ውጤት ሲያስገኙ አንዱ ጥናት ደግሞ ከሁለቱ የተለየ ውጤት አስገኝቷል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የውጤቶቹን ወጥ አለመሆን ነው፡፡፡ እንዲሁም

በጥናቶቹ ያልተዳሰሱ አንዳንድ ተላውጦዎች በዚህ ጥናት የተዳሰሱ ሲሆን በዚህም የጥናቶቹ ክፍተቶች ተሞልተዋል፡፡

የአንድነት (2010) ጥናት ላይ ታች እና ታች ላይ የንባብ ሞዴሎች አፍፊት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያላቸውን አስተዋጽዖ የመረመረ ጥናት ሲሆን ውጤቱ እንዳመለከተው ላይ ታች ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ጉልህ አስተዋጽዖ አለው፡፡ በተመሳሳይ በግሩም (2003) ጥናት ታች ላይ የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለው አስተዋጽዖ የተመረመረ ሲሆን በውጤቱም ሞዴሉ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው ተረጋግጧል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የእንግዳ (1992) ጥናት ላይ ታች ሞዴል የአፍፊት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ የፈተሸ ጥናት ሲሆን በጥናቱም ሞዴሉ አፍፊት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ጉልህ ሚና እንዳለው ተረጋግጧል፡፡

ከላይ የቀረቡት ሶስት ጥናቶች የሚያሳዩዋቸው ውጤቶች አንድ አይነት አይደሉም፡፡ የአንድነት (2010) ጥናት እና የግሩም (2003) ጥናት ያረጋገጡት ታች ላይ የንባብ ሞዴል አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የእንግዳ (1992) ጥናት እንዳመለከተው ላይ ታች የንባብ ሞዴል የአፍፊት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ጉልህ አስተዋጽዖ አለው፡፡ ይህም የሚያመለክተው በጥናቶቹ መካከል አንድ አይነት ውጤት እንደማይታይ ነው፡፡ እንዲሁም ሶስቱም ጥናቶች የተከናወኑት አፋቸውን በአማርኛ በፈቱ ተማሪዎች ላይ ሲሆን ይህ ጥናት የተከናወነው ደግሞ አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ በፈቱ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ሶስቱም ጥናቶች ያላካተቱት የማንበብ ተነሳሽነት በዚህ ጥናት ተካትቷል፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ተላውጦዎች በዚህ ጥናት መካተታቸው የጥናቶቹን ክፍተቶች ይህ ጥናት መሙላት ችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት መጠናዊ (Quantitative Research) ሲሆን ከጥናቱ ስልት አንጻር ደግሞ ከፊል ሙከራዊ (qusi-experimental) ስልትን በመተግበር ተከናውኗል፡፡ የጥናቱ አይነት መጠናዊ የሆነበት ምክንያት ለጥናቱ ያገለገሉት መረጃዎች የተሰበሰቡትና የተተነተኑት በመጠናዊ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች በመሆናቸው ነው፡፡ እንዲሁም የጥናቱ ስልት ከፊል ሙከራዊ የሆነበት ምክንያት ከንበብ ሞዴሎች ውስጥ ላይ ታች ሞዴልን በመጠቀም የማንበብ ክሒሎን በማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ከማሳደግ አንጻር የሞዴሉ ውጤታማነት በትክክለኛው የክፍል ውስጥ ዓውድ የተሞከረበት ጥናት በመሆኑ ነው፡፡

ጥናቱ ያተኮረበትን ንድፍ ተከትሎ የቅድመና የድህረ ሙከራ ፈተና አጠናን ስልት (Two Groups Pretest-Posttest design) ተከናወኗል፡፡ የዚህ አይነት የጥናት ሂደት ሁለት ቡድኖች ምንም ከመማራቸው በፊት በሚሰጣቸው ፈተናና አንድን ትምህርት በተለያዩ ማስተማሪያዎች (በዚህ ጥናት ዓውድ የማንበብ ሞዴል) ከተማሩ በኋላ በሚሰጣቸው ተመሳሳይ ፈተና የሚያስመዘግቡት የውጤት ልዩነት ያለበትን ደረጃ ለመፈተሽ የሚደረግ የአጠናን ሂደት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በዚህ ጥናት ሁለት ቡድኖች ተካትተዋል፡፡ ከሁለቱ ቡድኖች ውስጥ አንዱ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተተገበረባቸውን የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን ይዟል፤ እንዲሁም ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ልማዳዊው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ የተተገበረባቸውን የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ይዟል፡፡

## 3.2. የጥናቱ አካላይ

የዚህ ጥናት አካላዮች በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በጅማ ዞን በሚገኘው ጉማ ወረዳ የሚገኙ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ጥናቱ ትኩረት ያደረገውም በወረዳው ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሊሙ ሻይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በትምህርት ቤቱ በ2015 ዓ.ም በ10ኛ ክፍል በመማር ላይ

የነበሩ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ናሙናዎቹ ከጥናቱ አካላዮች ውሰጥ የተመረጡባቸው የንሞና ዘዴዎች ቀጥሎ ይቀርባሉ፡፡

## 3.3. የናሙናዎች አመራረጥ

### 3.3.1. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ

ይህ ጥናት የተከናወነው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት፣ በጅማ ዞን፣ ጉማ ወረዳ በሚገኘው ሊሙ ሻይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ይህ ትምህርት ቤት የተመረጠው በአመቺ የንሞና ዘዴ ሲሆን ይህም የተደረገበት ምክንያት ትምህርት ቤቱ አጥኚዋ በቋሚነት የምታስተምርበት ትምህርት ቤት በመሆኑ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ግብዓቶችን በቀላሉ ማግኘት ከማስቻሉም በተጨማሪ የጥናቱን ትምህርት በቅርበት ለመከታተል ስለሚያመቻት ትምህርት ቤቱ በጥናቱ ቦታነት ተመርጧል፡፡

### 3.3.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ይህ ጥናት የተከናወነው በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ የክፍል ደረጃው የተመረጠው በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ነው፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ የፈቱ የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋ ትምህርት በዚሁ ክፍል ብቻ የሚማቱ ሲሆን ከዚያ በላይ ያሉ ክፍሎች ግን አይማሪም። ከሁለቱ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ደግሞ 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርቱን የሚማሩበት የመጨረሻ የክፍል ደረጃ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ችግሩን መቅረፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አጥኚዋ በማመኗ የክፍል ደረጃው ለጥናቱ ተመርጧል፡፡

### 3.3.3. የተጠኚዎች አመራረጥ

የተጠናው ትምህርት ቤት እና የተማሪዎች የክፍል ደረጃ ከተመረጠ በኋላ በመቀጠል ተጠኚዎቹ ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ ይህ ጥናት ከፊል ሙከራዊ ጥናት በመሆኑ ምክንያት በተመረጠው ትምህርት ቤት ከሚገኙ 5 የ10ኛ ክፍል ምድቦች ውስጥ ሁለቱ መመረጥ አለባቸው፡፡ በመሆኑም በ5ቱ ምድቦች መካከል እጣ በማውጣት እጣው የወጣላቸው ሁለቱ

ምድቦች ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡ በዚህም መሰረት እጣው ለ10ኛ ‹B› እና ለ10ኛ ‹E› ወጥቶላቸው በተጠኚነት ተመርጠዋል፡፡ በ5ቱ ምድቦች ውስጥ በአማካይ ከ53 እስከ 56 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ ለጥናቱ በተመረጡት ሁለት ምድቦችም እያንዳንዳቸው 54 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡

በመቀጠልም በሁለቱ ምድቦች መካከል እንደገና ሌላ እጣ በማውጣት አንዱን ምድብ (10ኛ ‹E› ክፍል) በሙከራ ቡድንነት፣ እንዲሁም ሌላኛውን ምድብ (10ኛ ‹B› ክፍል) ደግሞ በቁጥጥር ቡድንነት ተመድበዋል፡፡ የተጠኚዎቹ አመራረጥ በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ የሆነበት ምክንያት የምድብ አመራረጡ ከአድሎ የጸዳ እንዲሆን ለማስቻልና 5ቱም የ10ኛ ክፍል ምድቦች በጥናቱ የመካተት እድላቸው እኩል እንዲሆኑ ለማስቻል ነው፡፡ እንዲሁም በሁለቱ ምድቦች መካከል ሁለተኛ እጣ ማውጣት ያስፈለገው የምድብ አመዳደቡን ከአድሎ የጸዳ እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

### 3.3.4. የማስተማሪያ ምንባቦች አመራረጥ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ጥናት የላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት በማሳደግ ረገድ ያለው ውጤታማነት ተመርምሯል፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ የማስተማሪያ ምንባቦችን መምረጥ አስፈላጊ ነው፡፡ የተመረጡት ምንባቦች ለአምስት ሳምንታት የሚሆኑ ሲሆኑ በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት ምንባቦች ለማስተማር የበለጠ ምቹ የሆኑት ተመርጠዋል፡፡ ምንባቦቹ የተመረጡትም በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ሲሆን ይህም የተደረገበት ምክንያት የጥናቱን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉና በተማሪዎች የማንበብ ተግባር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሌላቸውን ምንባቦች ለመምረጥ እንዲቻል ነው፡፡

## 3.4. የመማር ማስተማር ሒደት

ከላይ በተገለጸው መሰረት የማንበብ ክሒልን ለማስተማር ያገለገሉት ምንባቦች ተመርጠው፣ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው፣ ተገቢነታቸው ተገምግሞ የተስተካከለ የማስተማሪያ ማንዋል ከተዘጋጀ በኋላ ዋናዎቹ ተጠኚዎች እንዲማሩበት ተደርጓል፡፡ የተዘጋጀው የማስተማሪያ ማንዋል ለሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ማስተማሪያነት አገልግሏል፡፡ ይህም ማለት የሙከራ ቡድን ተማሪዎችም ሆኑ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የማንበብ ክሒልን የተማሩት በተዘጋጀው የማስተማሪያ ማንዋል ነው፡፡

የማስተማሪያ ማንዋሉ የተመረጡ ምንባቦችንና መለማመጃዎችን እንደሚይዝ ከላይ ተብራርቷል፡፡ ማንዋሉ ለሁለቱም ቡድን ተማሪዎች ማስተማሪያነት ያገለገለ ሲሆን የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ያነበቡባቸው ሞዴሎች ብቻ የተለያዩ ናቸው፡፡ የሁለቱም ቡድኖች ተማሪዎች በአንድ ማንዋል የተማሩበት ምክንያት የማስተማሪያ ማንዋሉ ከተለያየ በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል ስለሚችል ነው፡፡

ጥናቱ የራሱ ቋሚዎችና (constants) ተለዋዋጮች (variables) አሉት። ቋሚዎች የሚባሉት በሁለቱም ቡድኖች ተመሳሳይ የሆኑት ጉዳዮች ሲሆኑ በቡድኖቹ መካከል የሚለያዩት ደግሞ ተለዋዋጮች ናቸው። በዚህም መሰረት የጥናቱ ቋሚዎች የማስተማሪያ ማንዋል፣ የሚያስተምረው መምህር፣ የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ ፈተናዎች እና የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ የንባብ ሞዴሎች፣ የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ የጥናቱ ተለዋዋጮች ናቸው። ከተለዋዋጮቹ መካከል ሌላ ተለዋዋጭ ተጽእኖ የማያድርበት የማስተማሪያ ሞዴል ነጻ ተለዋዋጭ (independent variable) ሲሆኑ በሞዴሉ ተጽእኖ የሚደርስባቸው የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት እና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደግሞ ጥገኛ ተለዋዋጮች (dependent variables) ናቸው።

## 3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ እንደተገለጸው ለዚህ ጥናት ያገለገሉት መረጃዎች የተሰበሰቡት በቁጥር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የጥናቱ አይነት መጠናዊ ሊሆን ችሏል፡፡ እነዚህ መጠናዊ መረጃዎች የተሰበሰቡትም በሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ነው፡፡ ዘዴዎቹም ፈተናዎች እና የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተሰበሰቡት መረጃዎች ምን አይነት እንደሆኑና ዓላማዎቻቸው ምን እንደሆኑ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

### 3.5.1. ፈተናዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ላይ ታች የማንበብ ሞዴል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ተነሳሽነትት ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት መረጃ ከተሰበሰቡባቸው ዘዴዎች ውስጥ የመጀመሪያው ፈተና ነው፡፡ ፈተናው ያገለገለውም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን ነው፡፡ በዚህም መሰረት የጥናቱን ወሰን መሰረት ያደረጉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን የያዙ ሁለት ፈተናዎች በአጥኚዋ ተዘጋጅተዋል፤ አንዱ ቅድመ ፈተና ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ድህረ ፈተና ነው፡፡

በሁለቱም ፈተናዎች የተካተቱት የምንባብ አይነትና ብዛት፣ የጥያቄዎች አይነትና ብዛት፣ እንዲሁም የመመሪያዎች ብዛት ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በምንባብ አንድ ኢ-ልቦለዳዊ ገላጭ ጽሑፍ የቀረበ ሲሆን በሁለት መመሪያዎች የቀረቡ 15 ጥያቄዎች ወጥተውበታል፡፡ መመሪያ አንድ በምንባቡ ሀሳብ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት የሚመለሱ 5 ጥያቄዎችን ሲይዝ መመሪያ ሁለት ደግሞ በምንባቡ ሀሳብ መሰረት የሚመለሱ 10 የምርጫ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ ሁለተኛው ምንባብ አንድ አንቀጽ ሲሆን በውስጡ አምስት ክፍት ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ ከአንቀጹ በፊት ደግሞ በክፍት ቦታዎቹ ገብተው አንቀጹን የሚያሟሉ 8 ቃላት ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎቹም ከቀረቡት ቃላት በመምረጥ አንቀጹን እንዲያሟሉ ተጠይቀዋል፡፡ በመጨረሻም ስለግለሰብ ታሪክ የሚያወሳ አንደ አንቀጽ ቀርቧል፡፡ ከአንቀጹ በመቀጠልም ሁለት አጭር መልስ መጻፍን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

ፈተናዎቹ ከላይ በተገለጸው መልኩ በአጥኚዋ የተዘጋጁ ሲሆን ትክክለኛነታቸው (ተገቢነታቸው) በአማርኛ ቋንቋ መምህርነትና ፈተና አዘጋጅነት ልምድ ባላቸው መምህራን እና በጥናቱ አማካሪ ተገምግመዋል፡፡ በግምገማው መሰረትም እንደገና ተስተካክለው ለመሰጠት ዝግጁ ተደርገዋል፡፡ እንዲሁም የፈተናዎቹን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ በጥናቱ ያልተካተቱ 20 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ ከተፈተኑ በኋላም ፈተናዎቹ ታርመው የተገኘው ውጤት ተወስዶ ክሮምባች አልፋን በመጠቀም አስተማማኝነታቸው ተለክቷል፡፡ ክሮምባች አልፋው እንደሚያመለክተው ቅድመ ፈተናው 0.86 ሲሆን ድህረ ፈተናው ደግሞ 0.79 ሆኗል፡፡ በዚህም መሰረት ፈተናዎቹ አስተማማኝ መሆናቸው በመረጋገጡ ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች ተፈትነዋቸዋል፡፡

ቅድመ ፈተናውና ድህረ ፈተናው የየራሳቸው ዓላማዎች አሏቸው፡፡ ቅድመ ፈተናው የተሰጠው የጥናቱን ትምህርት ከመማራቸው በፊት ሲሆን ዓላማውም በሙከራ ቡድን እና በቁጥጥር ቡድን ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተመጣጣኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ተማሪዎቹ ትምህርቱን ከመማራቸው በፊት ተመጣጣኝ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳላቸው ማረጋገጥ ያስፈለገበት ምክንያት የተማሪዎቹ ችሎታ የሚበላለጥ ከሆነ በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር ነው፡፡

ሁለተኛው ፈተና ድህረ ፈተና ሲሆን የተሰጠውም ትምህርቱ ለ5 ሳምንታት (ለ10 ክፍለ ጊዜዎች) ተሰጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው፡፡ የዚህ ፈተና ዓላማም በትምህርቱ ወቅት ላይ ታች የንባብ ሞዴልን በመጠቀም የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ መሻሻል አለመሻሻሉን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም የንባብ ሞዴሉ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ ያለው አስተዋጽዖ ተመርምሮበታል፡፡

### 3.5.2. የጽሑፍ መጠይቅ

ሁለተኛው የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ያገለገለውም የተማሪዎቹን የማንበብ ተነሳሽነት ለመፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለመፈተሽ የማርያምወርቅ (2013) ያዘጋጁትን የጽሑፍ መጠይቅ በመውሰድና ለተጠኚዎቹ ተማሪዎች በሚያመች መንገድ በማስተካከል በጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የማርያምወርቅ ያዘጋጁት የጽሑፍ መጠይቅ በሊከርት ስኬል አዘገጃጀት ስርአት መሰረት የተዘጋጀ ሲሆን 30 ዝግ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ ለ30ዎቹ ጥያቄዎችም የመስማማት ደረጃዎችን የሚያመለክቱ ከ1 እስከ 4 ቁጥሮች ይገኛሉ፡፡ ተማሪዎቹ ለእያንዳንዱ ሀሳብ ያላቸውን የመስማማት ደረጃ በቁጥሮቹ እንዲገልጹ ተጠይቋል፡፡

ይህን የጽሑፍ መጠይቅ በቀጥታ የተወሰደ ሳይሆን መጠነኛ ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ የመጀመሪያው ማስተካከያ የተደረገው አማራጭ መልሶቹ ላይ ነው፡፡ የየማርያምወርቅ ጥናት አራት አማርጮች አሉት፡፡ ለዚህ ጥናት ለመውሰድ ግን አማራጮቹን ለማስፋት ሲባል አማራጮቹ አምስት ተደርገዋል፡፡ ሌላው የተሻሻለው ነገር የአንዳንድ ዓረፍተ ነገሮችን ያልተብራራ አገላለጽ አብራርቶ ማቅረብ ነው፡፡ ይህም የተደረገው የዚህ ጥናት ተጠኚዎች አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ የፈቱ በመሆናቸው አንዳንዶቹ ዓረፍተ ነገሮች የያዟቸው ሀሳቦች ግልጽ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ለተማሪዎቹ ግልጽ ሊሆን በሚችል መልኩ ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

የጽሑፍ መጠይቁ ከላይ በተገለጸው መልኩ ከተዘጋጀ በኋላ ልምድ ባላቸው መምህራንና በጥናቱ አማካሪ ተገምግሟል፡፡ በግምገማው የተሰጡትን አስተያየቶች መሰረት በማድረግ ተስተካክሎና በግልጽ ሊነበብ በሚችል ሁኔታ ታትሞ ለመሞላት ዝግጁ ተደርጓል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁን ዋናዎቹ ተጠኚዎች ከመሙላታቸው በፊት በጥናቱ ያልተካተቱ 20 ተማሪዎች ተመርጠው እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡ 20ዎቹ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ተወስዶም ክሮምባች አልፋን በመጠቀም የመጠይቁ አስተማማኝነት ተለክቷል፡፡ የክሮምባ አልፋ ውጤቱ እንደሚያመለክተው 0.81 ሲሆን ይህም የጽሑፍ መጠይቁ አስተማማኝ መሆኑን አመልክቷል፡፡ መጠይቁ አስተማማኝ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላም ዋናዎቹ ተጠኚ ተማሪዎች እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡

የጽሑፍ መጠይቁ የተሰጠው ሁለት ጊዜ ሲሆን አንዱ ከትምህርቱ በፊት እንዲሁም ሁለተኛው ደግሞ ከትምህርቱ በኋላ ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቁን ሁለት ጊዜ የተሞላውም ላይ ታች የንባብ ሞዴል በሙከራ ቡድን ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያመጣውን መሻሻል ከትምህርቱ በፊትና ከትምህርቱ በኋላ የተሞላውን በመውሰድ ለማነጻጸር እንዲመች ነው፡፡ በዚህም መሰረት በሁለቱም ቡድኖች የተካተቱት ተማሪዎች ከመማራቸው በፊት እና ከተማሩ በኋላ የጽሑፍ መጠይቁን እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡ በዚህም በቡድኖቹ መካከል የተፈጠረው የማንበብ ተነሳሽነት ልዩነት ተገምግሟል፡፡

## 3.6. የመረጃ አተናተን

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ለዚህ ጥናት ያገለገሉት መረጃዎች የተሰበሰቡት በፈተናዎች እና በጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ ከእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙት መረጃዎችም መጠናዊ መረጃዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎቹም እንዲሁ መጠናዊ መሆን ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው፡፡ ከመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ውስጥም ለዚህ ጥናት ያገለገለው የመተንተኛ ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት (Independent Samples t-test) ነው፡፡ ይህንን የመተንተኛ ዘዴ መጠቀም ያስፈለገውም የተማሪዎቹን የፈተናዎች ውጤትና የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ወስዶ በመተንተን በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች የፈተና ውጤትና የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡

ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኙት መረጃዎች ከመተንተናቸው በፊት በአይነት በአይነታቸው ተደራጅተዋል፡፡ ይህም ማለት አወንታዊ ሀሳቦችን ለያዙት ዓረፍተ ነገሮች የተሰጡት ምላሾች በቀጥታ ለመረጃ ትንተና ተወስደዋል፡፡ እንዲሁም አሉታዊ ሀሳብ ለሚይዙት ዓረፍተ ነገሮች የተሰጡት ምላሾች በተቃራኒያቸው ተወስደው በአንድ ላይ ሆነው የመረጃ ትንተናው ተከናውኗል፡፡ አሉታዊ ሀሳብ አመልካች ዓረፍተ ነገሮችን ምላሽ ተቃራኒ መውሰድ ያስፈለገበት ምክንያትም ሁሉም ሀሳቦች ተመሳሳይ አቅጣጫዎች እንዲኖሯቸው ለማስቻል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለአሉታዊ መጠይቆች የተሰጡት ምላሾች 1 ከሆነ 5፣ 2 ከሆነ 4፣ 3 ከሆነ 3፣ 4 ከሆነ 2፣ እንዲሁም 5 ከሆነ 1 ተደርገው ከተወሰዱ በኋላ የመረጃ ትንተናው ተከናውኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1. የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካትም ከፊል ሙከራዊ ጥናት የተከናወነ ሲሆን ለጥናቱ ያገለገሉ መረጃዎች በፈተና እና በጽሑፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡ በመቀጠልም የጥናቱን ዓላማዎች መሰረት በማድረግ የተሰበሰቡት መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡

### 4.1.1. ከቅድመ ፈተናው የተገኙት መረጃዎች ትንተና

የመጀመሪያው መረጃ የተሰበሰበው ቅድመ ፈተናን በመጠቀም ሲሆን ይህም የተሰጠው የጥናቱ ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት ነው፡፡ የቅድመ ፈተናው ዓላማ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች የጥናቱን ትምህርት ከመማራቸው በፊት ያላቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተመጣጣኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ ያስፈለገውም ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት ካለ በጥናቱ ትምህርት ላይም ሆነ በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር ነው፡፡ በመቀጠል የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከቅድመ ፈተናው ያስመዘገቡትን ውጤት በመውሰድ የተደረገው የመረጃ ትንተና ይቀርባል፡፡

*ሠንጠረዥ 1፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና*

| ቅድመ ፈተና | ቡድኖች | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት (Std. D) | የአማካይ ውጤት ልዩነት | የቲ-ዋጋ (T) | የነፃነት ደረጃ (df) | የጉልህነት ደረጃ (P) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ ቡድን | 54 | 14.33 | 6.066 | 2.06 | 1.82 | 106 | .072* |
| | የቁጥጥር ቡድን | 54 | 12.28 | 5.689 | | | | |

*P>0.05

ከላይ በሰንጠረዥ 1 የቀረበው ትንተና የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከቅድመ ፈተናው ያስመዘገቡትን ውጤት በመውሰድ የተከናወነ ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ነው፡፡ የመረጃ ትንተናው እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት (M) 14.33 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ 12.28 ነው፡፡ የሁለቱ ቡድኖች መደበኛ ልይይት (SD) እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች 6.07 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ደግሞ 5.69 ነው፡፡ እንዲሁም በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት መካከል የ2.06 ልዩነት ሲኖር የሚበልጠውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት ነው፡፡

የሙከራ ቡድን አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን አማካይ ውጤት መብለጡ ብቻውን ጉልህ ልዩነት መኖሩ አያመለክትም፡፡ ያለው (2006) እንደሚገልጹት በሁለት ቡድኖች መካከል የአማካይ ውጤት ልዩነት መኖሩን ማረጋገጥ የሚቻለው ቡድኖቹ ያስመዘገቡትን ውጤት በመውሰድ በባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትኖ የ‹ፒ› ዋጋ ከ0.05 የሚያንስ ከሆነና የ‹ቲ› ዋጋ ደግሞ ከ2.00 የሚበልጥ ከሆነ ነው፡፡ ነገር ግን የ‹ፒ› (P) ዋጋ ከ0.05 ከበለጠና የ‹ቲ› ዋጋ (T-value) ከ2.00 ካነሰ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት የለም፡፡ በዚህ መሰረት ከላይ የቀረበው የባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና እንደሚያመለክተው የ‹ፒ› ዋጋ ከ0.05 በልጦ 0.72 ሲሆን የ‹ቲ› ዋጋ ደግሞ ከ2.00 አንሶ 1.82 ሆኗል፡፡ ይህም የሚያመለክተው በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረበው የመረጃ ትንተና እንደሚያመለክተው የጥናቱን ትምህርት ከመማራቸው በፊት በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት የለም፡፡ ይህም የሚያሳው ከትምህርቱ በፊት የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተመጣጣኝ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የጥናቱን ትምህርት ለመስጠት አንዱ ምቹ ሁኔታ ነው፡፡ በመቀጠል ደግሞ ከቅድመ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡

## 4.1.2. ከቅድመ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የጽሑፍ መጠይቅ ሲሆን በመጀመሪያ የተሞላው የጥናቱ ትምህርት ከመጠቱ በፊት ነው፡፡ በቅድመ ትምህርቱ የተሞላው የጽሑፍ መጠይቅ ዓላማ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች የጥናቱን ትምህርት ከመማራቸው በፊት ያላቸው የንባብ ተነሳሽነት ተመጣጣኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ ያስፈለገውም ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል የንባብ ተነሳሽነት ልዩነት ካለ በጥናቱ ትምህርት ላይም ሆነ በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር ነው፡፡ በመቀጠል የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከትምህርቱ በፊት የሞሉትን የጽሑፍ መጠይቅ መረጃ በመውሰድ የተደረገው የመረጃ ትንተና ይቀርባል፡፡

***ሠንጠረዥ 2፡- የቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና***

| ቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ | ቡድን (group) | ናሙና (sample size) | አማካይ ውጤት (M) | መደበኛ ልይይት (SD) | መደበኛ የስህተት አማካይ (standard error mean) | የአማካይ ልዩነት (mean difference) | የ«ቲ» ዋጋ (t-value) | የነጻነት ደረጃ (Df) | ህባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት (P) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ ቡድን | 54 | 1.84 | .25 | .034 | -.03 | -.575 | 106 | .566* |
| | የቁጥጥር ቡድን | 54 | 1.87 | .22 | .029 | | | | |

*P>0.05

በሰንጠረዥ 2 የቀረበው የመረጃ ትንተና የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከትምህርቱ በፊት ከሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በመውሰድ የተደረገ ትንተና ነው፡፡ ከትምህርቱ በፊት የጽሑፍ መጠይቁን ማስሞላት ያስፈለገው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከጥናቱ ትምህርት በፊት ተመጣጣኝ የንባብ ተነሳሽነት መኖር አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ 30 ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን በሊከርት ስኬል አዘገጃጀት መሰረት የመስማማት ደረጃዎችን የሚወክሉ 5 ቁጥሮችን ይዟል፡፡ በመሆኑም 5 ከፍተኛ የመስማማት ደረጃን የሚያመለክት ሲሆን 1 ደግሞ ዝቅተኛውን ደረጃ ያሳያል፡፡ በዚህም ምክንያት ከፍተኛው አማካይ ውጤት 5፣ ዝቅተኛው ደግሞ 1 ሊሆን ችሏል፡፡

በሰንጠረዥ 2 የቀረበው ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ 1.84፣ መደበኛ ልይይቱ 0.25፣ መደበኛ የስህተት አማካዩ 0.034 ነው፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ 1.87፣ መደበኛ ልይይት 0.22፣ መደበኛ የስህተት አማካዩ 0.029 ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ከሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ በ0.03 እንደሚበልጥ ነው፡፡

የሁለቱ ቡድን አማካይ ውጤት ልዩነት ቢኖረውም ልዩነቱ ጉልህ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥም የባለሁለት ጫፍ ጉልህነቱን (ፒ) መመልከት ተገቢ ነው፡፡ ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ የሚገኘው ባለሁለት ጫፍ ጉልህነት (ፒ) 0.566 ሲሆን ይህም ከ0.05 ይበልጣ‹ቷ› ዋጋ -0.575 ሲሆን ይህም የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከሆነው ከ2.00 ያንሳል፡፡ ከዚህ ትንተና ውጤት መገንዘብ የሚቻለውም በሁለቱ ቡድኖች አማካይ መካከል ያለው መበላለጥ ጉልህ አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ከጥናቱ ትምህርት በፊት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት ተመጣጣኝ እንደሆነ በትንተናው ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ሁለት ትንተናዎች የተከናወኑት የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከጥናቱ ትምህርት በፊት ከተፈተኑት ፈተና እና ከሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በመውሰድ ነው፡፡ ይህም የተደረገው የጥናቱን ትምህርት ከማግራቸው በፊት በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ልዩነት እንደሌለ ለማረጋገጥ ነው፡፡ በተደረገው ትንተና እንደተረጋገጠውም የጥናቱ ትምህርት በፊት የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ተመጣጣኝ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ተነሳሽነት አላቸው፡፡ ይህም የጥናቱን ትምህርት ለማከናወን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ችሏል፡፡

## 4.1.3. ከድህረ ፈተናው የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከላይ በቀረበው ትንተና እንደተገለጸው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከጥናቱ ትምህርት በፊት ተመጣጣኝ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት አላቸው፡፡ በመቀጠልም የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች የጥናቱን ትምህርት ተምረዋል፡፡ ትምህርቱ የተሰጠውም ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች ላይ ታች የንባብ ሞዴልን በመጠቀም ሲሆን ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ ልማዳዊውን የንባብ ትምህርት አቀራረብ በመጠቀም ነው፡፡ ትምህርቱ ለ5 ሳምንታት ተሰጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላም የአንብቦ መረዳት ችሎታ መመዘኛ ድህረ ፈተና ተፈትነዋል፤ የጽሑፍ መጠይቅም ሞልተዋል፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል ከድህረ ፈተናው የተገኙ መረጃዎችን በመውሰድ የተከናወነው የመረጃ ትንተና ይቀርባል፡፡

ድህረ ፈተናው እንደ ቅድመ ፈተናው ሁሉ 22 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን 30 ነጥብ አለው፡፡ በፈተናው አራት መመሪያዎች ሲገኙ መመሪያ አንድ እውነት/ሐሰት በማለት የሚመለሱ 5 ጥያቄዎችን፣ መመሪያ ሁለት በምርጫ የሚመለሱ 10 ጥያቄዎችን፣ መመሪያ ሶስት ቃላትን በአንቀጽ ውስጥ በማስገባት የሚመለሱ 5 ጥያቄዎች፣ እንዲሁም መመሪያ አራት የምንባብን ሀሳብ በራስ አገላለጽ በመጻፍ የሚመለሱ 2 ጥያቄዎችን ይዘዋል፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ሰንጠረዥ የሚያመለክተው ከድህረ ፈተናው የተገኘውን ውጤት በመውሰድ የተከናወነውን ትንተና ነው፡፡

***ሠንጠረዥ 3፡- የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና***

| ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት | ቡድን (group) | ናሙና (sample size) | አማካይ ውጤት (M) | መደበኛ ልይይት (SD) | መደበኛ የስህተት አማካይ (standard error mean) | የአማካይ ልዩነት (mean difference) | የ«ቲ» ዋጋ (t-value) | የነጻነት ደረጃ (Df) | ህባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት (P) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ ቡድን | 54 | 16.4 | 3.98 | .542 | 3.33 | 3.46 | 106 | .001* |
| | የቁጥጥር ቡድን | 54 | 13.1 | 5.86 | .798 | | | | |

*P<0.05

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ 3 የሚገኘው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከድህረ ፈተናው ያስመዘገቡት ውጤት ተወስዶ የተደረ ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ነው፡፡ ትንተናው እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት 16.4 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 3.98 ነው፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድን አማካይ ውጤት 13.1 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 5.86 ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን አማካይ ውጤት በ3.33 እንደሚበልጥ ነው፡፡

ቀደም ሲል በተገለጸው የያለው (2006) ጥቆማ መሰረት የቡድኖቹን አማካይ ውጤት መበላለጥ በመመልከት ብቻ በቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ስለሆነም ልዩነቱ ጉልህ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የ‹ፒ›ን ዋጋ እና የ‹ቲ›ን ዋጋ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በሰንጠረዡ የቀረበው ትንተና እንደሚያመለክተው የ‹ፒ› ዋጋ ከ0.05 አንሶ 0.001 ሲሆን የ‹ቲ› ዋጋ ደግሞ ከ2.00 በልጦ 3.46 ሆኗል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት በጉልህ እንደሚበልጥ ነው፡፡

## 4.1.4. ከድህረ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከላይ የቀረበው ትንተና የተማሪዎቹ የደህረ ፈተና ውጤት ትንተና ሲሆን በትንተናውም በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት እንዳለ ተረጋጧል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ከጥናቱ ትምህርት በኋላ የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን በመውሰድ የተደረገው የመረጃ ትንተና ይቀርባል፡፡ ይህንን ትንተና ማድረግ ያስፈለገውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተማሩበት ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎቹን የንባብ ተነሳሽነት ምን ያህል ማሳደግ እንደሚችል ለማረጋገጥ ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ሰንጠረዥ የሚያመለክተው የድህረ ጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ ትንተናን ነው፡፡

*ሠንጠረዥ 4፡- የድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት*

| ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ | ቡድን (group) | ናሙና (sample size) | አማካይ ውጤት (M) | መደበኛ ልይይት (SD) | መደበኛ የስህተት አማካይ (standard error mean) | የአማካይ ልዩነት (mean difference | የ«ቲ» ዋጋ (t-value) | የነጻነት ደረጃ (Df) | ህባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት (P) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ ቡድን | 54 | 3.62 | .539 | .073 | .332 | 3.79 | 106 | .000* |
| | የቁጥጥር ቡድን | 54 | 3.29 | .351 | .048 | | | | |

*P<0.05

ከላይ በሰንጠረዥ 4 የቀረበው ትንተና የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ ከሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ በመውሰድ የተደረገ ትንተና ነው፡፡ የዚህ ትንተና ዓላማም ከትምህርቱ በፊት ተመጣጣኝ የነበረው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት ከጥናቱ ትምህርት በኋላ ጉልህ ልዩነት መማጣት አለመምጣቱን ለማረጋገጥ ነው፡፡

በሰንጠረዡ የቀረበው ትንተና እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ 3.62 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ደግሞ 3.29 ነው፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድን መደበኛ ልይይት 0.539 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መደበኛ ልይይት ደግሞ 0.351 ነው፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድን መደበኛ የስህተት አማካይ 0.073 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ደግሞ 0.048 ነው፡፡ ይህም ማለት የሙከራ ቡድን አማካይ ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ በ0.332 ይበልጣል ማለት ነው፡፡

የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎችን አማካይ የሚበልጠው በጉልህ ደረጃ መሆኑን ለማረጋገጥ የጉልህነት ደረጃውን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ የትንተናው ባለሁለት ጫፍ ጉልህነት (ፒ) እንደሚያመለክተው 0.000 ሲሆን የ‹ቲ› ዋጋ ደግሞ 3.79 ነው፡፡ ይህም የ‹ፒ› ዋጋ የጉልህነት መወሰኛ ከሆነው 0.05 እንደሚያንስና የ‹ቲ› ዋጋ ደግሞ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከሆነው 2.00 እንደሚበልጥ የሚያሳይ ሲሆን በዚህም ምክንያትም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው ልዩነት ጉልህ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከዚህም በመነሳት ከጥናቱ ትምህርት በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ያላቸው የንባብ ተነሳሽነት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት በጉልህ እንደሚበልጥ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ሲል በቀረቡት ሁለት የመረጃ ትንተናዎች ማረጋገጥ እንደተቻለው የጥናቱን ትምህርት ከመማራቸው በፊት የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ተነሳሽነት ተመጣጣኝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጥናቱ ትምህርት ከተሰጣቸው በኋላ በተፈተኑት ፈተና እና ከሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የአንብቦ መረዳት እና የንባብ ተነሳሽነት ልዩነት እንደተፈጠረ ተረጋግጧል፡፡ ጉልህ ብልጫውን ያመጡትም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ሲሆኑ ከዚህ ውጤት መገንዘብ የሚቻለውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተማሩበት ላይ ታች የንባብ ሞዴል የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ከተማሩበት ዘወትራዊው የንባብ ክሒል ማስተማሪያ ዘዴ የበለጠ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ተነሳሽነት ማሳደግ እንደሚችል ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ንዑስ ክፍል ለጥናቱ የተሰበሰቡት የፈተናዎችና የጽሑፍ መጠይቅ ፈተና የተሰበሰቡት መረጃዎች በአምስት ሰንጠረዦች ተተንትነዋል፡፡ በመጀመሪያ በቀረቡት ሁለት ሰንጠረዦች የተደረጉት ትንተናዎች እንደሚያመለክቱት የጥናቱ ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት የሙከራ ቡድን እና ቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ተነሳሽነት ተመጣጣኝ ነው፡፡ ይሁን እንጁ በሶስተኛና በአራተኛ በቀረቡት ሁለት ሰንጠረዦች የተደረገው የመረጃ ትንተና እንደሚያመለክተው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ያላቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ተመጣጣኝ አይደለም፤ የሙከራ ቡድን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በጉልህ ይበልጣል፡፡ ይህም የሚያለክተው ከጥናቱ ትምህርት በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት በጉልህ እንዳደገ ነው፡፡ በዚህ ትንተናም የጥናቱን ዓላማዎች በሙሉ ማሳካት ተችሏል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ይህ የመረጃ ትንተና ከሌሎች ጥናቶች አንጻር የሚያሳየው ውጤት ይብራራል፡፡

## 4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በተለዩዩ ጊዜዎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ትኩረት ያደረጉ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡ ጥናቶቹ እንደሚያመለክቱት የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በቀደሙ ጊዜዎችም ሆነ በቅርብ ጊዚያት የተደረጉት ጥናቶች የሚያመለክቱት የተማዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ በቅርብ ጊዜ ከተሰሩት መሰል ጥናቶች ውስጥ አስቴር (2010)፣ እንድሪስ (2009)፣ ዘውዱ (2008)፣ ግሩም (2003)፣ ታምራት (2003)፣ ብርሃን (2003) ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች ያረጋገጡትም የተማዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከሚጠበቀው በታች መሆኑን ነው፡፡

የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተለያዩ ምክንያቶች ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ በድሉ (1988)፤ የኔሰው (1990) እንግዳ (1992) እና Wainer & Piper (2010) የመሳሰሉት ቀደምት ጥናቶች እንዳመለከቱት በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ተላውጦዎች ውስጥ የማስተማሪያ ምንባቦች የተነባቢነት ችግር፣ የመምህራን የትምህርት አቀራረብ ችግር፣ የንባብ ሞዴሎች አጠቃቀም ችግር፣ የማንበብ ተነሳሽነት ችግር፣ ወዘተ. የመሳሰሉት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከእነዚህ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ተላውጦዎች ውስጥ የንባብ ሞዴል አጠቃቀም ችግር እና የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ችግር ጥናት ተደርጎባቸው መፍትሄ ቢሰጣቸው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ ጉልህ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው አጥኚዋ በማመን ይህንን ጥናት አከናውናለች፡፡

ጥናቱን ለማከናወን ስትነሳም ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የተለያዩ ጥናቶችን ለመዳሰስ ሞክራለች፡፡ ይሁን እንጂ ከጥናቶቹ የተገኙት ውጤቶች ወጥነት አይስተዋልባቸውም፡፡ እንግዳ (1992) ያደረጉት ጥናት እንደሚያመለክተው ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ግሩም (2003) እና አንድነት (2010) ባከናወኑት ጥናት የተገኘው ውጤት ታች ላይ የንባብ ሞዴል ከላይ ታች የንባብ ሞዴል የበለጠ የተማሪዎችን አንብቦ

የመረዳት ችሎታ ለማዳበር እንደሚጠቅም ያመለክታል፡፡ ይህም የጥናቶቹ ውጤት ወጥ አለመሆኑን ያመለክታል፡፡

ይህ ጥናት የተከናወነውም በእነዚህ ጉዳዮች መነሻነት ሲሆን ዓቢይ ዓላማውም ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር›› የሚል ነው፡፡ በዚህ ዓቢይ ዓላማ መነሻነትም ሶስት ዝርዝር ዓላማዎችን ማሳካት የተቻለ ሲሆን ቀደም ሲል የቀረበው የመረጃ ትንተና ከጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች አንጻር የሚያመለክተው ውጤት በዚህ ንዑስ ክፍል ይብራራል፤ እንዲሁም በተዛማጅ ጥናትነት ከተዳሰሱት ጥናቶች አንጻር ተብራርቶ ይቀርባል፡፡

የመጀመሪያው ዝርዝር ዓላማ ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር›› የሚል ነው፡፡ ይህንን ዝርዝር ዓላማ ለማሳካትም በተከናወነው ከፊል ሙከራዊ ጥናት ለጥናቱ የተመረጡት የሙከራ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የጥናቱን ትምህርት ከመማራቸው በፊት ቅድመ ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከፈተናው የተገኘው ውጤት ተወስዶም የመረጃ ትንተና ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም ከትምህርቱ በኋላ ድህረ ፈተና የተሰጣቸው ሲሆን ከድህረ ፈተናው የተገኘው ውጤት ተወስዶ ተተንትኗል፡፡ በመጨረሻም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቅድመ ፈተናው እና ከድህረ ፈተናው ያስመዘገቡት ውጤት ተወስዶ የመረጃ ትንተና ተደርጓል፡፡ የመረጃ ትንተናው የሚያመለክተው ውጤትም ቀጥሎ ይብራራል፡፡

ቅድመ ፈተናው 30 ነጥብ የያዘ ሲሆን የመረጃ ትንተናው እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (14.33) የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት (12.28) በ2.06 ይበልጣል፡፡ ምንም እንኳን የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት ልዩነት ቢኖርም የባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተናው ውጤት እንደሚያመለክተው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአማካይ ውጤት ልዩነት የለም ($t<2.00$፤ $p>0.05$)፡፡

ከጥናቱ ትምህርት በኋላ ደግሞ ድህረ ትምህርት ፈተና የተፈተኑ ሲሆን የድህረ ፈተና መረጃ ትንተናው እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት (16.4) ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት (13.1) በ3.33 ይበልጣል፡፡ እንዲሁም ይህ የአማካይ ውጤቱ ብልጫ ጉልህ እንደሆነ የባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተናው ያመለክታል ($t>2.00$፣ $p<0.05$)፡፡ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ የመጣው ከትምህርቱ በኋላ በተሰጠው የድህረ ፈተና ውጤት ሲሆን በቅድመ ፈተናው ግን የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ተመጣጣኝ አማካይ ውጤት ነበራቸው፡፡

የመጀመሪያው ዝርዝር ዓላማ ለማሳካት የተደረገው ትንተና እንዳመለከተው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ተመጣጣኝ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ቢኖራቸውም ከትምህርቱ በኋላ በተሰጣቸው ድህረ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት የሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጉልህ እንደሚበልጥ ነው፡፡ መበላለጡ የመጣው ከትምህርቱ በኋላ በመሆኑ ለውጡ የመጣው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በተማሩበት ላይ ታች የንባብ ሞዴል ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው በዚህ ትንተና ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ይህ ውጤት በተዛማጅ ጥናት ከተቃኙት ጥናቶች ውስጥ ከእንግዳ (1992) ጥናት ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በግሩም (2003) እና በአንድነት (2010) ጥናቶች ከተገኘው ውጤት ጋር ይለያያል፡፡ በእንግዳ (1992) የተደረገው ጥናት የሚያመለክተው ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው ሲሆን በግሩም (2003) እና በአንድነት (2013) የተደረገው ጥናት የሚያመለክቱት ደግሞ ታች ላይ የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው ነው፡፡

በግሩም ጥናት የተገኘው ውጤት ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር መመሳሰሉ ከተለያዩ ጉዳዮች አንጻር ጥናቱ ሰፊ ዓውድ እንዲኖረው አስችሏል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የሁለቱ ጥናቶች ውጤት ከዚህ ጥናት የተለየ ውጤት ማስገኘታቸው ሊፈጠር የቻለው የተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ

ቋንቋን ጨምሮ የነበሩት የተለያዩ የተላውጦዎች ልዩነት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም በርዕሰ ጉዳዩ ተጨማሪ ጥናቶችን ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ መርዳት አለመርዳቱን ማረጋገጥ›› የሚል ነው፡፡ ይህንን ዝርዝር ዓላማ ለማሳካትም በተከናወነው ከፊል ሙከራዊ ጥናት ለጥናቱ የተመረጡት የሙከራ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የጥናቱን ትምህርት ከመማራቸው በፊት የንባብ ተነሳሽነታቸውን የሚለካ የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ተወስዶም የመረጃ ትንተና ተከናውኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው የሚያመለክተው ውጤትም ቀጥሎ ይብራራል፡፡

በመረጃ ትንተናው ክፍል ከቀረቡት አምስት ትንተናዎች ውስጥ ሁለቱ የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች የተተነተኑባቸው ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች ትንተና የተከናወነው ከትምህርቱ በፊት ከተሞላው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በመውሰድ ነው፡፡ የተደረገው የመረጃ ትንተና እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ (1.84) ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ (1.87) በ0.03 ያንሳል፡፡ ይሁን እንጂ የውጤት ልዩነቱ ጉልህ እንዳልሆነ የባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተናው ያመለክታል ($t<2.00$፣ $p>0.05$)፡፡

የንባብ ተነሳሽነትን የሚመለከተው ሁለተኛው የመረጃ ትንተና ክፍል ከድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች የተተነተኑበት ነው፡፡ ይህንን ትንተና ማከናወን ያስፈለገበትም ከጥናቱ ትምህርት በኋላ በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የንባብ ተነሳሽነት ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም ላይ ታች የንባብ ሞዴል በሙከራ ቡድን ተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት ላይ ለውጥ ማምጣት አለማምጣቱ ተመርምሮበታል፡፡

የድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ የመረጃ ትንተና እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ (3.62) ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ (3.29) በ0.332 ይበልጣል፡፡ እንዲሁም ይህ የአማካይ ብልጫ ጉልህ እንደሆነ የባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተናው ያመለክታል (t>2.00፣ p<0.05)፡፡ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ የመጣው ከትምህርቱ በኋላ ከተሞላው የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ሲሆን በቅድመ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ ምላሽ የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ተመጣጣኝ አማካይ ነበራቸው፡፡

ሁለተኛውን የጥናቱን ዝርዝር ዓላማ ለማሳካት የተደረገው ትንተና እንዳመለከተው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከትምህርቱ በፊት ተመጣጣኝ የንባብ ተነሳሽነት ቢኖራቸውም ከትምህርቱ በኋላ ከሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ በመውሰድ የተደረገው የመረጃ ትንተና የሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነት በጉልህ እንደሚበልጥ ነው፡፡ መበላለጡ የመጣው ከትምህርቱ በኋላ በመሆኑ ለውጡ የመጣው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በተማሩበት ላይ ታች የንባብ ሞዴል ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው በዚህ ትንተና ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህም ሁለተኛው የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ መሳካት ችሏል፡፡

ይህ ጥናት በምዕራፍ ሁለት ከተቃኙት ተዛማጅ ጥናቶች የሚለይበት አንዱ ተላውጦ የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት ማካተቱ ነው፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል በቀረቡት ሶስት ተዛማጅ ጥናቶች የታየው የንባብ ተነሳሽነትን ያለማካተት ክፍተት በዚህ ጥናት ሊሞላ ችሏል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት የተከናወነው ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽዖ ለመመርመር ነው፡፡ ለዚህም ከፊል ሙከራዊ ጥናት የተከናወነ ሲሆን ለጥናቱ ያገለገሉ መረጃዎች በፈተና እና በጽሑፍ መጠይቅ ተሰብስበው በባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ከተተነተኑ በኋላ በገለጻ ተብራርተዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ እንደሚያለክተው ከጥናቱ ትምህርት በፊት የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ተመጣጣኝ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ነበራቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከጥናቱ ትምህርት በኋላ የሙከራ ቡድን

ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በጉልህ ይበልጣል፡፡ ይህ ውጤት የሚያመለክተውም ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት በጉልህ እንደሚያሳድግ ነው፡፡

ከዚህ ውጤትም መካከል ሞዴሉ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ በእንግዳ (1992) በተደረገው ጥናት ከተገኘው ውጤት ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በግሩም (2003) እና በአንድነት (2010) ከተገኘው ውጤት ይለያል፡፡ እንዲሁም በሁሉም ጥናት ያልተካተተው የንባብ ተነሳሽነት በዚህ ጥናት በመካተቱ የቀደምት ጥናቶቹ ውጤት ሰፊ ዓውድ እንዲኖረው አድርጓል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# የጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ እና አስተያየት

## 5.1. የጥናቱ ማጠቃለያ

ይህ ጥናት አንድ ዓቢይ ዓላማ ሁለት ዝርዝር ዓላማዎች ሲኖሩት ዓቢይ ዓላማውን መሰረት ያደረጉ ሁለት መላምቶች ተዘጋጅተው በተከናወነው ከፊል ሙከራዊ ጥናት የተገኘውን ውጤት በመመርኮዝም አንዱ ተቀባይነት ሲያገኝ ሌላኛው ደግሞ ውድቅ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ሶስቱን ዝርዝር ዓላማዎች መሰረት በማድረግ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች የተዘጋጁ ሲሆን በተደረገው ከፊል ሙከራዊ ጥናት ጥያቄዎቹ መልስ አግኝተዋል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ‹‹ላይ ታች  የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር›› የሚል ነው፡፡ ከዚህ ዓቢይ ዓላማ በመነሳት ሁለት መላምቶች የተዘጋጁ ሲሆን እነሱም ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ለማዳበር ጉልህ አስተዋጽዖ አለው›› እና ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ለማዳበር ጉልህ አስተዋጽዖ የለውም›› የሚሉ ናቸው፡፡ ከሁለቱ መላምቶች አንዱ ተቀባይነት አግኝቶ ሌላኛው ውድቅ እንዲሆን ከፊል ሙከራዊ ጥናት ተከናውኗል፡፡

ከሁለቱ መላምቶች አንዱ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሁለት የ10ኛ ክፍል ምድቦች ተመርጠው ጥናቱ ተከናውኗል፡፡ የተመረጡት ቡድኖች የጥናቱን ትምህርት ከመማራቸው በፊት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን የሚመዝን ቅድመ ፈተናመም ተፈትነዋል፤ የንባብ ተነሳሽነታቸውን የሚለካ የጽሑፍ መጠይቅም ሞልተዋል፡፡ ከቅድመ ፈተናውና እና ከቅድመ የጽሑፍ መጠይቁ የተገኙት መረጃዎችም በባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትነው ውጤቱ እንዳመለከተው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ተመጣጣኝ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ተነሳሽነት አላቸው፡፡

ተማሪዎቹ ተመጣጣኝ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት እንዳላቸው ከተረጋገጠ በኋላ አንዱ ምድብ (የሙከራ ቡድን) በላይ ታች የንባብ ሞዴል ሲማሩ ሌላኛው ምድብ (የቁጥጥር ቡድን) ደግሞ በልማዳዊው የትምህርት አቀራረብ ተምረዋል፡፡ ትምህርቱን ለአምስት ሳምንታት ከተማሩ በኋላም የድህረ ፈተና ተፈትነዋል፤ የጽሑፍ መጠይቅም ሞልተዋል፡፡ ከፈተናውና ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኙት መረጃዎችም በባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ተተንትነዋል፡፡ የመረጃ ትንተናው እንዳመለከተውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የድህረ ፈተና አማካይ ውጤት እና የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በጉልህ ይበልጣል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት በጉልህ እንደሚበልጥ ነው፡፡

ይህንን የመረጃ ትንተና ውጤት መሰረት በማድረግም ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ተነሳሽነት ለማዳበር ጉልህ አስተዋጽዖ አለው›› የሚለው አማራጭ መላምት ተቀባይነት ሲያገኝ ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ለማዳበር ጉልህ አስተዋጽዖ የለውም›› የሚለው አልቦ መላምት ደግሞ ውድቅ ተደርጓል፡፡ በዚህም የጥናቱን ዓቢይ ዓላማ ማሳካት ተችሏል፡፡

ይህ ጥናት ከላይ ከተገለጸው ዓቢይ ዓላማ በመነሳት ሶስት ዝርዝር ዓላማዎችን ማሳካት ችሏል፡፡ የመጀመሪያው ዝርዝር ዓላማ ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር›› የሚል ነው፡፡ ይህንን ዝርዝር ዓላማ ለማሳካትም የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከድህረ ፈተመና ያስዘገቡት ውጤት ተወስዶ የመረጃ ትንተና ተከናውኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው እንዳመለከተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የድህረ ፈተና ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የድህረ ፈተና ውጤት በጉልህ ይበልጣል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎቹ በላይ ታች የንባብ ሞዴል በመማራቸው ምክንያት በተማሩት ትምህርት በጉልህ ለውጥ ማምጣት እንደቻሉ ነው፡፡

ሁለተኛው ዝርዝር ዓላማ ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ መርዳት አለመርዳቱን ማረጋገጥ›› የሚል ነው፡፡ ይህንን ዝርዝር ዓላማ ለማሳካትም የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከጥናቱ ትምህርት በኋላ ከሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በመውሰድ የመረጃ ትንተና ተከናውኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው እንዳመለከተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ በጉልህ ይበልጣል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በላይ ታች የንባብ ሞዴል በመማራቸው ምክንያት የንባብ ተነሳሽነታቸው በጉልህ እንዳሸለ ነው፡፡

የመጨረሻው ዝርዝር ዓላማ ‹‹የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቧቸው ቅድመ ፈተና እና ድህረ ፈተና መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ›› ይህንን ዓላማ ለማሳካትም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቅድመ ፈተናው ያስመዘገቡትን ውጤት እና ከድህረ ፈተናው ያስመዘገቡትን ውጤት በመውሰድ በባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡ የመረጃ ትንተናው ውጤት እንዳመለከተውም የተማሪዎቹ የድህረ ፈተና ውጤት ከቅድመ ፈተና ውጤታቸው በጉልህ ይበልጣል፡፡

## 5.2. የጥናቱ መደምደሚያ

ይህ ጥናት ከላይ በተገለጸው መንገድ ተከናውኖ ዓላማዎቹን ማሳካት ችሏል፡፡ የጥናቱ ዓላማዎች በመሳካታቸውም ሶስት የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ አግኝተዋል፡፡ ከዚህም በመሳት በጥናቱ ሶስት ዋና ዋና መደምደሚያዎች ላይ መድረስ ተችሏል፡፡ በዚህ ጥናት የተደረሰባቸው መደምደሚያዎችም ቀጥሎ ይቀርባሉ፡፡

የመጀመሪያው የጥናቱ ጥያቄ ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ አስተዋጽኦ ይኖረው ይሆን?›› የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠትም የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ከድህረ ፈተናው ያስመዘገቡትን ውጤት በመውሰድ የመረጃ ትንተና ተከናውኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው የሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት

በጉልህ እንደሚበልጥ ነው፡፡ ይህም ለመጀመሪያው ጥያቄ መልስ የተሰጠ ሲሆን ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጉልህ ማሳደግ ይችላል›› የሚል መደምደሚያ ተደርሷል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ ጥያቄ ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ  አስተዋጽዖ አለው?›› የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠትም የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ ከሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በመውሰድ የመረጃ ትንተና ተከናውኗል፡፡ የትንተናው ውጤት እንደሚያመለክተውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ በጉልህ ይበልጣል፡፡ ይህም ለሁለተኛው ጥያቄ መልስ የሰጠ ሲሆን ከዚህም በመነሳት ‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ አለው›› የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡

የመጨረሻው የጥናቱ ጥያቄ ‹‹የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት ቅድመ ፈተና እና ድህረ ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለ?›› የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠትም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቅድመ ፈተናውና ከድህረ ፈተናው ያስመዘገቡትን ውጤት በመውሰድ የመረጃ ትንተና ተከናውኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው እንዳመለከተው የተማሪዎቹ የድህረ ፈተና ውጤት ከቅድመ ፈተናው ውጤት በጉልህ ይበልጣል፡፡ በዚህም ሶስተኛው ጥያቄ መልስ ያገኘ ሲሆን ከዚህም በመሳት ‹‹የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ያስመዘገቡት የድህረ ፈተና ውጤት የቅድመ ፈተና ውጤታቸውን በጉልህ ይበልጣል›› የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ቀደም ሲል የተገለጹት ውጤቶች ተገኝተዋል፤ በተገኘው ውጤትም ለሶስቱ የጥናቱ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ተችሏል፡፡ ጥያቄዎቹ መልስ ማግኘታቸውን ተከትሎም የሚከተሉት ሶስት መደምደሚያዎች ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

- ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ከዘወትራዊው የንባብ ሞዴል በጉልህ የሚበልጥ አስተዋጽዖ አለው፡፡

- ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን የንባብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ከዘወትራዊው የንባብ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴ በጉልህ የሚበልጥ አስተዋጽዖ አለው፡፡

- ላይ ታች የንባብ ሞዴልን በመጠቀም የተማሩት ተማሪዎች የድህረ ፈተና አማካይ ውጤት የቅድመ ፈተናውን አማካይ ውጤት በጉልህ ይበልጣል፡፡

## 5.3. የጥናቱ አስተያየት

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ምዕራፍ አንድ ስር ‹‹የጥናቱ ጠቀሜታ›› በሚለው ንዑስ ርዕስ ይህ ጥናት ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ለሚያሰለጥኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አሰልጣኞች፣ ለመማሪያና ለማስተማሪያ ቁሳቁስ አዘጋጆችና ለሌሎች አጥኚዎች ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ደግሞ ለእነዚህ አካላት ያለው ጠቀሜታ እውን ይሆን ዘንድ የሚጠቀሙባቸውን መንገዶች የሚያሳክቱ አስተያየቶች ይጠቆማሉ፡፡

የመጀመሪያው አስተያየት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ማረጋገጥ እንደተቻለው ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ አለው፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንባብ ትምህርትን ሲያስተምሩ ላይ ታች የንባብ ሞዴልን ተጠቅመው ቢያስተምሩ የተማሪዎቻቸውን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ተነሳሽነት ማሳደግ ይችላሉ፡፡

ሌላው አስተያየት ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ለሚያሰለጥኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አሰልጣኞችን የሚመለከት ነው፡፡ አሰልጣኞቹ ከዚህ ጥናት የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ የሚያሰለጥኗቸው እጩ መምህራን ላይ ታች የንባብ ሞዴልን የሚጠቀሙባቸውን የተመለከተ ስልጠና ቢሰጧቸው መልካም ነው፡፡ በተጨማሪም የሞዴሉን አተገባበር በማስረዳት በማስተማር ስራቸው እንዲጠቀሙ ግንዛቤ ቢፈጥሩላቸው መምህራኑ ውጤታማ የንባብ ትምህርትን እንዲያከናውኑ እድል ይፈጠርላቸዋል፡፡

የመማሪያና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን የሚያዘጋጁ ሰዎች ቁሳቁሶቹን ሲያዘጋጁ ላይ ታች የንባብ ሞዴልን ከግምት ውስጥ በማስገባት ቢያደርጉ መልካም ነው፡፡ ይህም ማለት አዘጋጆቹ የንባብ ትምህርትን ለማስተማር በሚያካትቷቸው ትምህርቶች ውስጥ መምህራን ላይ ታች የንባብ ሞዴልን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው፣ ተማሪዎችም ሞዴሉን በመጠቀም እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ገለጻ ቢሰጧቸው መልካም ነው፡፡ የቁሳቁስ አዘጋጆቹ ይህንን ማድረግ ከቻሉ መምህራኑና ተማሪዎቹ ላይ ታች የንባብ ሞዴልን በመጠቀም ውጤታማ የንባብ ትምህርት ማከናወን ይችላሉ፡፡

የመጨረሻው አስተያየት ሌሎች አጥኚዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ጥናት የተከናወነው በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ሁለት የ10ኛ ክፍል መድቦችን በመምረጥ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት በሌሎች አካባቢዎችና በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን ላይወክል ይችላል፡፡ በመሆኑም ሌሎች አጥኚዎች በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የሚማሩና በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ላይ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የናሙናዎችን ቁጥር በመጨመር ተጨማሪ ጥናቶችን ቢያጠኑ ከዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት ሰፊ ዓውድ ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት መከናወኑ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አሰልጣኞች፣ ለመማሪያና ማስተማሪያ ቁሳቁሶች አዘጋጆችና ለሌሎች አጥኚዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ እነዚህ አካላት በዚህ ጥናት ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ ከላይ በተሰጡት አስተያየቶች መሰረት የተለያዩ ተግባራትን ቢያከናውኑ መልካም ነው፡፡ አስተያየቶቹን እንዲያገኟቸው ደግሞ የጥናቱ ባለቤት የሆነው ጅማ ዩኒቨርሲቲ በድረ ገጹና በተለያዩ መንገዶች ይህንን ጥናት ተደራሽ ቢያደርገው መልካም ነው፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


መአዛ ደጀኔ፡፡ (1999)፡፡ *በ9ኛ ክፍል የንባብ ትምህርት አሰጣጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ በአዲስ አበባ በሚገኙ ሦስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኤም ኤ ዱግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ *በስነ ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

አንድነት እድገቱ፡፡ (2010)፡፡ ‹‹*በበቶሙለ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ከላይ ታች እና ከታች ላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት ክሂል ያላቸውን አስተዋጽኦ በማነፃፀር የተሻለውን ሞዳል ለመለየት 7ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ጥናት*››፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ለማስተርስ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡

እንግዳ ዘውዴ፡፡ (1992)፡፡ *“የቶፕ ዳውን” የንባብ ማስተማሪያ* ሞዳል በአማርኛ አንብቦ *መረዳት* ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡ *አዲስ* አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኤም ኤ *ዲግሪ ማሟያ* ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)፡፡

የማርያምወርቅ አበበ፡፡ (2013)፡፡ *የመደገፍ* ብልሃቶች የተማሪዎችን አንብቦ *የመረዳት* ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነትን ለማዳበር ያላቸው ሚና (በ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)፡፡ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ግሩም ጥበቡ፡፡ (2003)፡፡ “የታች ላይ” የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሒልን ለማዳበር ያለው ውጤታማነትና ተተግባሪነት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)፡፡

Ahmadi, M. R., & Gilakjani, A. P. (2012). *Reciprocal teaching strategies and their impacts on English reading comprehension*. Theory and Practice in Language Studies, 2(20532060).

Al-Bargi, A. ((2017). *The impact of Scaffolding Strategies in Enhancing Reading Comprehension Skills of University Students*. English Language Institute King Adulaziz University.

Alderson, J. (2000). *Assessing reading*. Cambridge, UK: Cambridge University.

Anderson, R. C., Hiebert, E., Scott, J., & Wilkinson, I. (1985). *Becoming a nation of readers:* The report of the Commission on Reading. Champaign, IL: Center for the Study of Reading.

Cunningham, A. E., & Stanovich, K. E. (1998). *What reading does for the mind*. *American Educator,* 22, 8-15.

Dornyei, Z. (2001). *Teaching and Researching Motivation*. Harlow: Longman. Acquisition. Honolulu, HI: University of Hawaii Press.

Field, J. (2004). *Psycholinguistics: The key Concepts* .London: Routledge

Grabe, W. ( 1991). *Current developments in second language reading research*. TESOL Quarterly, 25, 3, 375-406. doi: 10.2307/3586977.

Grellet, F. (1986). *New Developments in teaching reading comprehesion skill to Ef lerners.* New York: Cambridge University Press, New York.

Guthrie, J. T., & Wigfield, A. (2000). *Engagement and motivation in reading. In M.L. Kamil, P. B. Mosenthal, P. D. Pearson, and R. Barr (Eds.),* Handbook of Reading Research. (Vol. III, pp. 403-22). Mahwah, NJ: Lawrence Erlbaum Associates.

Harmer, J. (2002 ). *The Practice of English Language Teaching*: 3rd edition. Harlow: Pearson Education Ltd.

_______(2007). *How to teach English*. London: Longman.

Koule, L. (1996), *Methodology of education research*. (2nd ed,) Uiks Publishing House Pvt. Ltd.

Meiryun, Y. (1995). “Teaching Efficient EFL Reading” Inkral, Tomas Leds. Teacher Development Making the Right Moves. Washington, DC. PP.

Nunan, D. (1991). Language teaching methodology: A textbook for teachers. Prentice Hall.

Nuttall, **c** (1982). Teaching Reading skill in foreign language London: Heinemann Educational Book Ltd.

Pardede, P. (2006). *A Review on Reading Theories and its Implication to the Teaching of Reading*. Universitas Kristen Indonesia.

RAND Reading Study Group. (2002). *Reading for Understanding toward an R&D Program in Reading Comprehension.* 2002. U. S.: RAND. Journal Pendidikan dan Persajaran. EDUKASI.

Smith, F. (1985). *Reading*. Cambridge University press.

Takase, A. (2007). *Japanese High School Studen Motivation for Extensive L2 Reading.* Reading in a Foreign Language, 19(1), 1—18.

Ur, P. (1996). Aresearch in language teaching practice and theory. Cambridge: Cambridge Universty press.

USAID/Ethiopia. (2003). Improving Quality of Primary Education Program (USAID/IQPEP) in Ethiopia. Addis Ababa.

Wallace, M. (1991). *Training foreign language teachers*: A Reflective Approach. Cambridge: Cambridge University Press.

Wang, M. ( 2009). *Effects of metacognitive reading strategy instruction on EFL high school students' reading comprehension, reading strategies awareness, and reading motivation*. (Doctoral Dissertation). Retrieved from http://www.ufl.edu.

Williams, E. (1984). *Reading in the Language Classroom*. London: Macmillan Publishers.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፤ የቅድመ ትምህርት ፈተና

**አጠቃላይ** *መመሪያ፡-* ይህ ፈተና የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመለካት የተዘጋጀ ነው፡፡ የፈተናው ጥያቄዎች የቀረቡት በአራት መመሪያዎች ነው፡፡ ፈተናው አራት ምንባቦችን የያዘ ሲሆን ከእያንዳንዱ ምንባብ የተውጣጡ 22 ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡ መመሪያ አንድ እውነት ወይም ሀሰት በማለት የሚመለሱ 5 ጥያቄዎችን፣ መመሪያ ሁለት በመምረጥ የሚመለሱ 10 ጥያቄዎችን፣ መመሪያ ሶስት በክፍት ቦታ ቃላትን በመሙላት የሚመለሱ 5 ጥያቄዎችን፣ እንዲሁም መመሪያ አራት አጭር መልስ በመጻፍ የሚመለሱ 2 ጥያቄዎችን ይዘዋል፡፡ መመሪያዎቹ በሚያዙት መሰረት ተገቢ መልስ በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ በመጻፍ መልሱ፡፡

ለፈተናው የተፈቀደ ጊዜ፡- 1፡30

ፈተናው የሚጀመርበት ጊዜ፡- ከረፋዱ 3፡00

ፈተናው የሚጠናቀቅበት ጊዜ፡- ከረፋዱ 4፡30

*መልካም ፈተና!*

# ምንባብ አንድ

ጸሐፊ ተጨንቆና ተጠቦ የድርሰት አጻጻፍ ስርዓትና ህግጋትን ጠብቆ አንድ የጽሑፍ ስራ ያዘጋጃል፡፡ ነገር ግን ያዘጋጀው የአንባቢን የንባብ ስሜት የማይቀሰቅስ ከሆነ አድራሻ እንደሌለው ደብዳቤ ተቀባይ በማጣት የያዘውን እንደያዘ ይቀራል፡፡ ስለዚህ የንባብ ስሜት ወይም ፍላጎት ለመቀስቀስና አንባቢ እጅ ገብቶ እንዲነበብና መልዕክቱ እንዲጣጣም ታስቦ የሚቀርብ ጽሑፍ ከሁሉ አስቀድሞ የአንባበቢን የንባብ ስሜትና ፍላጎት ወጥሮ እንዲይዝና ስሜቱን ኮርኩሮ እንዲያነቃቃው ተደርጎ መዘጋጀት አለበት፡፡

ጸሐፊ አንድ ጽሑፍ ለማዘጋጀት በሚነሳበት ጊዜ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሱን መጠየቅ አለበት፡፡ ጥያቄዎቹም የጽሑፉ አንባቢ ምን ዓይነት ሰው ነው? ዕድሜው ምን ያህል ነው? ሙያውስ? የትምህርት ደረጃውና የኑሮ አቋሙስ ምን ዓይነት ነው? ለምሰነዝረው ሃሳብ ምን ዓይነት ግምት ይኖረው ይሆን? የቋንቋዬ አጠቃቀም፣ የዓረፍተ ነገሮቼ አሰካክ፣ የአንቀጾቼ አደራደር ሃሳቤን በግልጽ ያስተላልፉሉ? ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ጸሐፊ እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን ራሱን በመጠየቅ በጽሑፉ ላይ የሚያሰፍረው ሃሳብ በሁነኛ መልሶች የተመሰረተ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም አንድ ጸሐፊ ሃሳቡ እንዲሳካለት ከፈለገ የተደራሲያኑን አጠቃላይ ፍላጎት ለማሟላት የተቻለውን ጥናትና ምርምር ከማድረግ መቦዘን የለበትም፡፡ እዚህ ላይ ጸሐፊው የአንባቢዎቹን ፍላጎት እንዴት አድርጎ ማወቅ ይችላል? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል፡፡ መልሱ ግን ቀላል አይደለም፡፡ ባጭሩ ብዙ መጨነቅ ብዙ መጠበብ ይኖርበታል፡፡

አንድ ደራሲ ከተደራሲያኑ ጋር የሰመረ መግባባት ሊፈጥር የሚችለው በጽሑፉ የሰፈረው ሃሳብ ተነባቢነት ሲኖረውና ለመረዳትም የሚቻል ሲሆን ነው፡፡ ይህንን የመግባባት ሂደት የተሳካ ለማድረግ ደግሞ የአንባቢን ፍላጎት፣ ምኞትና ዓላማ፣ የሚያዝናናውንና የሚያስደስተውን እንዲሁም ቁም ነገር የሚያስጨብጠውን ነገር ለማወቅ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

አብዛኞዎቹ ጸሐፊዎች በዕውቀትም ሆነ በኑሮ ደረጃ ከራሳቸው ጋር ለሚመሳሰሉ አንባቢያን መጻፍ አስቸጋሪ አይሆንባቸውም፡፡ ጥሩ ጸሐፊ ሃሳቡን በወረቀት በሚያሰፍርበት ጊዜ ተደራሲያኑን ከዓይነ ህሊናው አይለይም፡፡ በዕውቀት ደረጃቸውም ሆነ በኑሮ ገጠመኞቻቸው ለተለያዩ ሰዎች በሚጽፍበት ጊዜ የተለያዩ አንባቢያንን ለማስተናገድ የሚችልበትን መንገድ በሃሳቡ ከመቀየስ አይቦዝንም፡፡

**(አማረ ማሞ፡፡ የቀለም ጠብታ፣ 1976ዓ.ም፣ ገጽ፣ 167-170)**

**መመሪያ አንድ፡- ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 ከላይ ከቀረበው ምንባብ የወጡ ዓረፍተ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ዓረፍተ ነገሮቹ የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆነ ‹‹ሐሰት›› ብላችሁ በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ በመጻፍ መልስ ስጡ (5 ነጥብ)፡፡**

1. ደራሲ ተነባቢ ድርሰት ለመጻፍ የአዕምሮ ጭንቀት ሊይዘው ይችላል፡፡
2. አንድ ደራሲ ጽሑፉ የሚነበብለት የራሱን ፍላጎት ብቻ ሲያንጸባርቅ ነው፡፡›
3. በመጀመሪያው አንቀጽ …ወጥሮ መያዝ… ሲል አስገድዶ ማስነበብ ማለቱ ነው፡፡
4. ማንኛውም ሰው ተነባቢ የሆነ ድርሰት መጻፍ የሚችለው በልምምድ ነው፡፡
5. አንባቢ ያጣ ጽሑፍና ጸሐፊ የሌለው ደብዳቤ አንድ ናቸው፡፡

**መመሪያ ሁለት፡- ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 6 እስከ 15 ለቀረቡት ጥያቄዎች ቀደም ሲል ያነበባችሁት ምንባብ በያዘው ሀሳብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ መርጣችሁ በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ በጻፍ መልሱ (10 ነጥብ)፡፡**

6. የመጀመሪያው አንቀጽ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?
   ሀ. ጽህፈት የትጉሃን ስራ ነው፡፡
   ለ. ማንኛውም ሰው ሊያነብ ይችላል፡፡
   ሐ. ደብዳቤ ከጽሁፍ አይነቶች አንዱ ነው፡፡
   መ. የአጻጻፍ ህግን መጠበቅ ለጽሁፍ ጥራት በቂ ነው፡፡
7. አንድ ጸሃፊ አንባቢያንን ለማወቅ ጥያቄዎችን በማንሳት ራሱን ለምን ይጠይቃል?
   ሀ. የአንባቢውን ስሜት የማይኮረኩር ጽሁፍ ለመጻፍ፣
   ለ. የንባቢውን ስሜትና ፍላጎት የሚይዝ ጽሁፍ ለመጻፍ፣
   ሐ. ራሱን በጥያቄ ለማዝናናት፣
   መ. ለጥያቄዎቹ እውነተኛ መልስ ለመስጠት፣
8. ጥናትና ምርምር ለማድረግ የማይቦዝን ደራሲ በስራው ምን ሊገጥመው ይችላል?
   ሀ. የአንባቢያንን ፍላጎት ሊያሟላ ይችላል፡፡
   ለ. ብዙ መጨነቅና መጠበብ ሊገጥመው ይችላል፡፡
   ሐ. የሚጽፈው ጽሑፍ ተነባቢ ሊሆን ይችላል፡፡
   መ. ሀ እና ሐ መልስ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
9. አንድ ደራሲ ከተደራሲያኑ ጋር መግባባት ሊፈጥር የሚችለው እንዴት ነው?
   ሀ. አንባቢው የሚያዝናናውን ጉዳይ ሲያውቅ፣
   ለ. አንባቢው የሚፈልገውን ቁምነገር ሲያውቅ፣
   ሐ. የአንባቢውን ምኞት ሲያውቅ፣
   መ. ሁሉም መልሶች ናቸው
10. አንድ ደራሲ ጽሁፍ ከመጻፉ በፊት ቅድሚያ ማሰብ ያለበት ነገር ምንድን ነው?
    ሀ. ስለገበያ ሁኔታው ሐ. ስለጥናትና ምርምር፣
    ለ. ስለአንባቢያን ፍላጎት፣ መ. ስለመጨነቅና መጠበብ፣
11. ‹‹<u>የሰመረ</u> መግባባት…›› በሚለው ሐረግ የተሰመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍቺ__________ነው፡፡
    ሀ. የተሰመረ ለ. የተደራጀ ሐ. መልካም መ. የሻከረ

12. አንድ የጽሁፍ ይዘት ለአንባቢ ተጨባጭና ቀጥተኛ የሆነ ጠቀሜታ እንዳይኖረው የሚያደርገው ምንድን ነው?

ሀ. ደራሲው የሚጠቀምባቸው ቃላትና ሃረጋት ግልጽነት የጎደላቸው ከሆነ፣

ለ. ጸሐፊው ይዞት የተነሳው ሃሳብ ከአንባበቢው ፍላጎት ጋር የማይገናኝ ከሆነ፣

ሐ. የደራሲውን ፍላጎት ብቻ የሚያንጸባርቅ ከሆነ፣

መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ፡፡

13. ከሚከተሉት ውስጥ ከአንድ ጥሩ ጸሐፊ የሚጠበቀው የትኛው ነው?

ሀ. ለማን እንደሚጽፍ ለማወቅ መቦዘን፣

ለ. የድርሰት አጻጻፍ ህግጋት ማወቅ፣

ሐ. ለራሱ የሀሳብ ፍላጎት ብቻ ትኩረት መስጠት፣

መ. ቁምነገረኛ ሃሳቦች ላይ እንጂ አዝናኝ ሃሳቦች ላይ አለማተኮር፣

14. ምንባቡ የቀረበበት የድርሰት አጻጻፍ ስልት ምንድን ነው?

ሀ. ተራኪ ለ. አስረጂ ሐ. ስዕላዊ መ. አከራካሪ

15. ከሚከተሉት ውስጥ ለምንባቡ የተሻለ ሊሆን የሚችለው ርዕስ የትኛው ነው?

ሀ. ለማን እንጽፋለን ለ. ለምን እንጽፋለን

ሐ. እንዴት እንጽፋለን መ. ምን እንጽፋለን

**መመሪያ ሶስት፡- ቀጥሎ በቀረበው አንቀፅ ከተራ ቁጥር 16 እስከ 20 ያሉ የተጓደሉ ክፍት ቦታዎችን ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት 8 ቃላት ውስጥ እንዳንዱን ክፍት ቦታ በትክክል ሊያሟላ የሚችለውን ቃል በመምረጥ በተራ ቁጥሩ መሰረት በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ ፊደሉን ብቻ በመጻፍ መልሱ (5 ነጥብ)፡፡**

## ምንባብ 2

**ሀ. ውጣ ውረዶች** **ሐ. የተጨረሰ** **ሠ. በቀመስን**

**ለ. የጉልበት** **መ. ተሳትፏቸው** **ረ. በጨለፍን**

**ሰ. ቅልጥፍናቸው** **ሸ. ያካበቱት**

እድሜ መስታወት ነው፡፡ ይህ አባባል ሰዎች እድሜያቸው እየገፋ ሲሄድ ከህይወት_ ______(8) ልምድና እውቀት ጥልቅና ሰፊ መሆኑን ለማመልከት የሚነገር ነው፡፡ አረጋዊያን በአያሌ የኑሮ________(9) ተፈትነው ያለፉ የእድሜ ባለጸጎች ናቸው፡፡ ከህይወት ልምዳቸው ጥቂት___________(10) ቁጥርም ሚዛን የሚደፉ ቁም ነገር አናጣም፡፡ አረጋዊያን በእድሜ መግፋት የተነሳ አካላዊ____________(11) እየደከመ ቢሄድም እንኳን አቅማቸው በፈቀደው መጠን በተለያዩ ስራዎች ተሰማርተው እናገኛቸዋለን በዚህ እድሜያቸው በማህበረሰቡ ጎልቶ የሚታየው___________(12) ሳይሆን አእምሯዊ ሀብታቸው ነው፡፡

**መመሪያ አራት፡- ቀጥሎ የቀረበውን አንቀጽ በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ በተራ ቁጥር 21 እና 22 ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ አጭር መልስ በመጻፍ መልሱ (10 ነጥብ)፡፡**

## ምንባብ 3

ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ እንዲለብሱት የተሰጣቸውን ብርድ ልብስ ተልትለው በመቀጣጠል ገመድ ካዘጋጁ በኋላ ተንጠልጥለው ከእስር ቤት አመለጡ፡፡ ከዚያም በገጠሩ የጣሊያን በረሃ ውስጥ በመጓዝ ላይ እያሉ አንድ ሽማግሌና ልጁ ከብቶች ሲጠብቁ አገኟቸው፡፡ ምግብ ለምነው ከበሉ በኋላ እነአብዲሣ የሽማግሌውን ፈረስና መሳሪያ እንዲሰጧቸው ጠየቋቸው፡፡ ሰዎቹ ለመስጠት ፍቃደኛ ስላልሆኑላቸው ቀምተው ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ ሌ/ኮ/ አብዲሣ በሀገራቸው ጀግና እንደ ነበሩት ሁሉ በጣሊያን ሀገርም እጅ አልሰጡም፡፡ በጣሊያን ሀገር ከፋሽስት ጦር ጋር ከሚዋጉ ሌሎች አርበኞች ጋር ተቀላቅለው ከጠላት ጋር እየገጠሙ በሚያስገኙት ድል ዝነኛ እየሆኑ ሄዱ፡፡ ሌሎች አርበኞችም ጀግንነታቸውን አይተው የአንድ ክፍለ ጦር አዛዥ አድርገው ሾሟቸው፡፡ በተለያዩ የጦር ግንባሮች ተሰልፈው በማሸነፋቸውም ዝናቸው በየቦታው ተሰማ፡፡

21. ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ያከናወኗቸውን ዋና ዋና ተግባራት በአጭሩ ግለጹ፡፡

22. ሌፍተናንት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ከሀገራቸው ውጭ ቢታሰሩም ከእስር ቤቱ በማምለጥ ለክብር መብቃታቸው ስለሳቸው ማንነት የሚያሳየውን በአጭሩ አስረዱ፡፡

# አባሪ ሁለት፤ የድህረ ትምህርት ፈተና

**አጠቃላይ** *መመሪያ*፡- *ይህ ፈተና* የአንብቦ *መረዳት* ችሎታን ለመለካት የተዘጋጀ ነው፡፡ የፈተናው ጥያቄዎች የቀረቡት በአራት *መመሪያዎች* ነው፡፡ ፈተናው አራት ምንባቦችን የያዘ ሲሆን ከእያንዳንዱ ምንባብ የወጡ 2 ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡ *መመሪያ* አንድ እውነት ወይም ሀሰት በማለት የሚመለሱ 5 ጥያቄዎችን፣ *መመሪያ* ሁለት በመምረጥ የሚመለሱ 10 ጥያቄዎችን፣ *መመሪያ* ሶስት በክፍት ቦታ ቃላትን በመሙላት የሚመለሱ 5 ጥያቄዎችን፣ እንዲሁም *መመሪያ* አራት አጭር መልስ በመጻፍ የሚመለሱ 2 ጥያቄዎችን ይዘዋል፡፡ *መመሪያዎቹ* በሚያዙት መሰረት ተገቢ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ በመጻፍ መልሱ፡፡

ለፈተናው የተፈቀደ ጊዜ፡- 1፡30

ፈተናው የሚጀመርበት ጊዜ፡- ከረፋዱ 3፡00

ፈተናው የሚጠናቀቅበት ጊዜ፡- ከረፋዱ 4፡30

*መልካም ፈተና!*

# ምንባብ አንድ

ልቦወለድ በእንግሊዘኛ ቋንቋ "Novel" የሚባለውን የስነ ጽሁፍ ዘርፍ እንዲወክል የተመረጠ ስነ ጽሁፋዊ ስያሜ ነው፡፡ ‹‹ልብወለድ ምንድን ነው?›› ለሚለው የመነሻ ጥያቄ አንድ ቁጥር ያለና ሁሉን አቀፍ ብያኔ መስጠት አዳጋች ይሆናል፡፡ ይህ የስነ ጽሑፍ ዘርፍ ከታየበት ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ የተነሱ አያሌ የስነ ጽሁፍ ሀያሲያንና ደራሲያን ከሚያደርጉት የስነጽሁፍ ገለጻና ጥናት፣ ከሚሰጡት ስነ ጽሁፋዊ ትንታኔና ዓላማ ምክንያት፣ ባህሪና አቅጣጫ አንጻር ሀሳባቸውን ሰጥተውበታል፡፡

ልቦለድ ከደራሲው ምናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ የሰውን ህይወት ልዩ ልዩ መልኮች በተመሳስሎ ለመቅረፅ የሚችልና በቁሙ ግን እውነት ያልሆነ የኪነ ጥበብ ስራ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ልቦለድ በቁሙ እውነት አይደለም ሲባል የተተረከው የገፀ ባህሪያት ህይወት በእውነተኛው ዓለም በእርግጥ የተፈፀመ ታሪኩ በሚፈቅደው ዘመንና ቦታ እንዳለ የታየ አይደለም ለማለት ነው፡፡ ልቦለድ በብዙ ሀያሲያንና የስነፅሁፍ ጠቢባን አስተያየት የልቦለድ ምንነት ባጭር ብያኔ ለማሳወቅ ከመሞከር የልቦለድን ባህርያትና ለህልውናው መሠረት የሆኑትን ፍሬ ነገሮች/አላባውያን መግለጽ የተሻለ ነው፡፡ ዋና ዋናዎቹ የልቦለድ ፍሬ ነገሮች (አላባውያን) የሚባሉት ታሪክ፣ መቼት፣ ጭብጥ ገፀ ባህርያት፣ ግጭት፣ ትልም/ሴራ እና የትረካ አንጻር ናቸው፡፡

የልቦለድ አላባውያን ለየብቻቸው ተነጥለው የሚቀርቡ ሳይሆን እርስ በእርሳቸው ተሰናስለውና ተደጋግፈው ልቦለዱን እውን የሚያደርጉ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ገጸ ባህርያት በልቦለዱ ውስጥ የሚገለጸውን ሀሳብ የሚያንጸባርቁና የግሀዱ ዓለም ሰዎችን የሚወክሉ ባለታሪኮች ሲሆኑ ታሪክ ደግሞ በገጸ ባህርያቱ አማካኝነት የሚከናወኑ ተግባራትን ያመለክታል፡፡ ገጸ ባህርያቱ በሚፈጥሯቸው ታሪኮች ምክንያት አለመግባባት ይፈጠራል፡፡ ይህ የገጸ ባህርያት አለመግባባት ግጭት የተባለውን የልቦለድ አላባ ያመለክታል፡፡

ግጭት የሚጎላው በትልም (ሴራ) ነው፡፡ ትልም ግጭትን የሚያጎላበት ምክንያትም ግጭት የተፈጠረባቸውን ሁነቶች በሙሉ በምክንያትና በውጤት ተሰናስለው የሚቀርቡበት በመሆኑ ነው፡፡ ሁሉም አላባውያን ተሰናስለው የሚቀርቡበትን ጊዜና ቦታ አጣምሮ የሚይዘው የልቦለድ አላባ ደግሞ መቼት ሲሆን ታሪኩ ለተደራሲያን የሚቀርብበት መንገድ ደግሞ የትረካ አንጻር ነው፡፡ እነዚህ አላባውያን ተሰናስለው ልቦለድን የሚፈጥሩት ደራሲያን በውስጣቸው ያለውን ሀሳብ ወይም መልእክት ለማስተላለፍ ነው፡፡ ይህ የልቦለድ ዋና መልእክት ወይም ማዕከላዊ ጉዳይ ደግሞ ጭብጥ በመባል ይታወቃል፡፡

ከላይ የቀረቡት የልቦለድ አላባውያን ልቦለዱ እንዲፈጠር ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ ለልቦለዱ እውን መሆን ባላቸው ሚና አንዱ ከሌላው አይበልጥም፣ አያንስም፡፡ ምክንያቱም ልቦለዱ ምሉዕ የሚሆነው ሁሉም አላባውያን ተሰናስለው በልቦለዱ ሲካተቱ ነው፡፡ ከመካከላቸው አንዱ አላባ ከጎደለ ልቦለዱ ምሉዕነት የጎደለው **ቁንጽል** ይሆናል፡፡ በመሆኑም አንድ የልቦለድ ደራሲ የሰዎችን ትኩረት መሳብ የሚችል ልቦለድ ለመጻፍ የእያንዳንዱን የልቦለድ አላባ መሰረታዊ ባህርያት በሚገባ መረዳት አለበት፡፡ ከመረዳትም ባሻገር የአላባውያኑን መሰረታዊ ባህርያት በጠበቀ መልኩ ማዘጋጀትና በልቦለዱ ውስጥ ማካተት አለበት፡፡

**መመሪያ አንድ፡- ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 ከላይ ከቀረበው ምንባብ የወጡ ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡ በምንባቡ  መሰረት ዓረፍተ ነገሮቹ የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆነ ‹‹ሐሰት›› ብላችሁ በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ በመጻፍ መልስ ስጡ (5 ነጥብ)፡፡**

1. ልቦለድ ሁሉንም የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ሊያስማማ የሚችል ወጥ ብያኔ አለው፡፡
2. ገጸ ባህርያት በግሀዱ ዓለም ልዩ ልዩ ተግባራትን የሚያከናውኑ ግለሰቦች ናቸው፡፡
3. ግጭትን አጉልቶ ማውጣት የሚችለው የልቦለድ አላባ ትልም ይባላል፡፡
4. በልቦለድ ውስጥ ሁሉንም አላባውያን ማካተት የግድ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡
5. የልቦለድ አላባውያን በልቦለድ ውስጥ ለየብቻቸው ተነጣጥለው ይቀርባሉ፡፡

**መመሪያ ሁለት፡- ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 6 እስከ 15 ለቀረቡት ጥያቄዎች ቀደም ሲል ያነበባችሁት ምንባብ በያዘው ሀሳብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ መርጣችሁ በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ መልሱ (10 ነጥብ)፡፡**

6. ከሚከተሉት ውስጥ በአንደኛው አንቀጽ የቀረበውን ሀሳብ የሚያመለክተው የትኛው ነው?
   ሀ. የተለያዩ ባለሙያዎች ለልቦለድ የየራሳቸውን ብያኔ ሰጠተዋል፡፡
   ለ. ልቦለድ ከሌላው የስነ ጽሑፍ ዘርፍ የሚለየው በርካታ ባህርያት አሉት፡፡
   ሐ. ልቦለድ ለመዝናናትና ሀሳብ ለማስተላለፍ ይጻፋል፡፡
   መ. ልቦለድ የተለያዩ ጭብጦችን ይይዛል፡፡
7. ልቦለድን በቁሙ እውነት አይደለም ያስባለው ምክንያት ምንድን ነው?
   ሀ. ገፀ ባህርያት ህይወት በእውኑ ዓለም የታየ አለመሆኑ
   ለ. የአንድ ሰው ታሪክ ከልደቱ እስከ ሞቱ መተረኩ
   ሐ. የልቦለዱ ህይወት ከሰው ልጆች ህይወት ተመሳስሎ አለመቅረቡ
   መ. የሚተረከው የሰውን ልጆች እውነተኛ ታሪክ አለመሆኑ
8. የገጸባህሪያት አለመሰማማትና አለመግባባት ከልቦለድ አላባውያን መካከል የትኛውን ያመለክታል?
   ሀ. ገጸ ባህርይ  ለ. ግጭት  ሐ. ታሪክ  መ. መቼት
9. የልቦለድ ታሪክን በምክንያትና ውጤት በቅደም ተከተል የሚያቀርብ አላባ ምን ይባላል?
   ሀ. ታሪክ  ለ. መቼት  ሐ. ትልም  መ. ግጭት
10. የልቦለድ ታሪክ የሚከናወንበትን ጊዜና ቦታ የሚያመለክት የልቦለድ አላባ ምን ይባላል?
   ሀ. ትልም  ለ. ታሪክ  ሐ. ገጸባህርይ  መ. መቼት
11. ልቦለድ የግሀዱ ዓለም ነጸብራቅ ያስባለው ምኑ ነው?
   ሀ. ታሪኩ በሰው ልጆች የሚፈጸምና መሆኑ
   ለ. የተወከሉትን ገጸባህሪያት በትክክል ስለሚታወቁ
   ሐ. የልቦለዱ ታሪክ በእውነተኛው ዓለም ሊከሰት የሚችል መሆኑ
   መ. የሰዎችን ህይወት የማያንጸባርቅ መሆኑ
12. ከሚከተሉት ውስጥ ልቦለድን በተመለከተ ትክክለኛ ሀሳብ የያዘው የትኛው ነው?
   ሀ. የፈጠራ ስራ ነው  ለ. በቁሙ እውነት ያልሆነ ታሪክ ነው
   ሐ. አላባውያን ያካተተ ነው  መ. ሁሉም መልሶች ናቸው
13. ምንባቡ የቀረበው በየትኛው የአጻጻፍ ዘዴ ነው?

ሀ. በተራኪ ለ. በገላጭ ሐ. በአመዛዛኝ መ. በስእላዊ

14. አንድ ልቦለድ ምሉዕነት ሊጎድለው የሚችለው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. የልቦለዱ ታሪክ በአጭሩ ሲቋጭ

ለ. የልቦለዱ ግጭት አሳማኝ ሳይሆን ሲቀር

ሐ. ሁሉንም የልቦለድ አላባዊያን ሳያካትት ሲቀር

መ. በብዙ አንባቢያን ሳይነበብ ሲቀር

15. ‹‹**ቁንጽል**›› የሚለው ቃል ዓውዳዊ ፍቺ___________ነው፡፡

ሀ. ቁልል ለ. ጎዶሎ ሐ. የተሟላ መ. ቅያሪ

**መመሪያ ሶስት፡- ቀጥሎ በቀረበው አንቀፅ ከተራ ቁጥር 16 እስከ 20 ያሉ የተጓደሉ ክፍት ቦታዎችን ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት 8 ቃላት ውስጥ እንዳንዱን ክፍት ቦታ በትክክል ሊያሟላ የሚችለውን ቃል በመምረጥ በተራ ቁጥሩ መሰረት በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ ፊደሉን ብቻ በመጻፍ መልሱ (5 ነጥብ)፡፡**

## ምንባብ 2

**ሀ. ማስታወቂያ** **ሐ. ሽርክና** **ሠ. ዘላቂነት**

**ለ. ጫና** **መ. አሀድ** **ረ. እውቅና**

**ሰ. መቋረጥ** **ሸ. መለምለም**

ጋብቻ ባህላዊ፣ ማህበራዊ ስነ ምግባራዊ መሰረት ያለው የግለሰቦች ጥምረት ነው፡፡ ዋነኛ ግቡም የህብረተሰብ መዋቅር መሰረታዊ (16) _________________ የሆነውን ቤተሰብን መመስረትና የማህበረሰቡን ህልውና (17) _____________ ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ተጋቢዎች አንድ ህጋዊና ማህበራዊ ተቋም ለመመስረት የሚያስችላቸውን (18) ___________ ሲመሰርቱ አባል ለሆኑበት ማህበራዊ ይፋዊ (19) __________ ይሆን ዘንድ ልዩ የጋብቻ ስነ ስርዓትን ያዘጋጃሉ፤ ያከብራሉ፡፡ ማህበረሰቡም ለዚህ ሽርክና (20) _________________ ይሰጣል፡፡

**መመሪያ አራት፡- ቀጥሎ የቀረበውን አንቀጽ በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ በተራ ቁጥር 21 እና 22 ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ አጭር መልስ በመጻፍ መልሱ (10 ነጥብ)፡፡**

## ምንባብ 3

ጀኔራል ታደሰ ብሩ ፋሽስቶች ኢትዮጵያን ለቀው እስኪወጡ ድረስ ሲዋጉ እንደነበረ ይነገራል፡፡ ኢትዮጵያ እንዳዲስ ስትመሰረትም የምስረታ ኮሚቴው አባል በመሆን በባሻነት ተሹመዋል፡፡ በ1934 በምስራቅ ኢትዮጵያ፣ በሐረርጌ አከባቢ ወደ ግንባር ተልከው በመሄድ የጦሩ መቶ አለቃ ምክትል በመሆን ተሹመው አገልግለዋል፡፡ በዚሁ ዘመን ወደ ሆለታ ገነት ስልጠና ማእከል ገብተው በተለያዩ የጦር ስልቶች ስልጠና በመውሰድ በተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውረው ሲታገሉ ነበር፡፡ ከ3 ዐመታት በኋላ በ1937 ወደ ማዕከሉ ተመልሰው በመምህርነት ሲያገለግሉ እንደነበር ታሪክ ይዘክራል፡፡ ጀኔራል ታደሰ ብሩ በ33 አመታቸው የሌተና ኮሎኔልነትን ማዕረግ በማግኘት በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈጥኖ ደራሽ ወይም ልዩ ኃይል የተባሉ ፖልሶችን አሰልጥነው አስመርቀዋል፡፡

21. ጀነራል ታደሰ ብሩ ያከናወኗቸውን ዋና ዋና ተግባራትና በህላፊነት የመሯቸውን ተቋማት በአጭሩ ግለጹ፡፡

22. ጀነራል ታደሰ ብሩ በ33 ዓመታቸው ሌተና ኮሎኔልነት ማዕረግ መቻላቸው በስራ ዓለም ስላላቸው ማንነት የሚገልጸውን በአጭሩ አስረዱ፡፡

# አባሪ ሶስት፤ የማንበብ ተነሳሽነት ለመለካት የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ

**ውድ ተማሪዎች፡-** የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ **‹‹ላይ ታች የንባብ ሞዴል የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ተነሳሽነት ለማዳበር ያለው ሚና (አፈ ፈት ባልሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)››** በሚል ርዕስ ለሚደረገው ምርምር መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ለሌላ ዓላማ አይውልም፡፡ የአንተ/ቺ ትክክለኛ ምላሽ የጥናቱ ውጤት ተቀባይነት እንዲኖረው ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ምላሾችህ/ሽ የራስህን/ሽን አቋም በትክክል የሚያንፀባርቁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ጥያቄዎችን በትዕግስት አንብበህ/ሽ በማጤን እንድትመልስ/ሽ ስጠይቅ ለምታደርግልኝ/ጊልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ሀ. የትኛውንም መልስ ብትሰጥ/ጪ ትክክል ወይም ስህተት አለመሆኑን ከግንዘቤ ውስጥ አስገባ/ቢ፡፡

ለ. ጥያቄዎቹን ለመመለስ ከሌላ ጓደኛ ጋር መመካከር አይፈቀድም፡፡

ሐ. ለምላሽህ/ሽ መነሻ የምታደርገው/ጊው በአሁኑ ወቅት ያለህን/ሽን ግንዛቤና የማንበብ ተግባር ብቻ ነው፡፡

**መመሪያ፡-** ቀጥሎ የማንበብ ተነሳሽነትን የተመከቱ 30 ሀሳቦች ቀርበዋል፤ በእያንዳንዱ ሀሳብ በቀኝ በኩል ደግሞ ከ1 እስከ 5 ቁጥሮች አማራጮች ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ተነሳሽነታችሁን የሚገልጽላችሁ አማራጭ ላይ በማክበብ መልሱ፡፡ ቁጥሮቹ የሚወክሏቸው መግለጫዎች ቀጥሎ ይቀርባሉ፡፡

1. **በጣም እስማማለሁ**
2. **እስማማለሁ**
3. **ለመወሰን ያስቸግረኛል**
4. **አልስማማም**
5. **ፈፅሞ አልስማማም**

| ተራ ቁጥር | ጥያቄ | የስምምነት ደረጃ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ማንበብን በሚመለከት ወደፊት የተሻለ ስራ እንደምሰራ አውቃለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 2. | ለራሴ ጥሩ አንባቢ ነኝ ብዬ አስባለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 3. | በክፍል ውስጥ ከሌሎች ተማሪዎች በበለጠ በማንበብ እማራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 4. | ከባድ ነገሮችን በማንበብ ዘወትር እማራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 5. | መምህሩ ስለአንድ አስደሳች ነገር ሲገልፁልኝ ስለነገሩ ብዙ አነባለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6. | ስለሚስቡኝ ርዕሰ ጉዳዮች ለመማር አዳዲስ መረጃዎችን በማንበብ አውቃለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 7. | የዘወትር ምርጫዬ ስለሆነው ጉዳይ ብዙ ለመማር አነባለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 8. | ስለአዳዲስ ነገሮች ማንበብ እወዳለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 9. | በማነብበት ጊዜ በአእምሮዬ ስዕል እፈጥራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 10. | ጥሩ መጻሕፍት ከሰዎች ጋር ጓደኝነት እንደፈጠርኩ ያህል ስሜት ያሳድሩብኛል፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 11. | ለእኔ ጥሩ አንባቢ መሆን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 12. | ከምሰራቸው ሌሎች ተግባሮች ጋር ሲወዳደር ጥሩ አንባቢ መሆን ለእኔ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 13. | የማንበብ ተግባሬን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሜ መጨረስ እወዳለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 14. | ከሚነበቡ ጽሁፎች ለሚነሱ ጥያቄዎች ብቸኛ መላሽ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 15. | ስሜ በጥሩ አንባቢዎች ዝርዝር ውስጥ ቢሰፍር ለእኔ ጠቃሚ ነው፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 16. | ከጓደኞቼ በበለጠ በማንበብ ተግባር ጠንክሬ ለመስራት ፈቃደኛ ነኝ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 17. | አንዳንድ ጊዜ ጓደኞቼ ጥሩ አንባቢ እንደሆንኩ ይነግሩኛል፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 18. | የማንበብ ውጤቴ ስላለኝ የማንበብ ጥንካሬ ጥሩ አመላካች ነው፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 19. | የማንበብ ውጤቴን ለማወቅ ሁል ጊዜም ወደፊት አስባለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 20. | የማንበብ ውጤቴን ለማሻሻል አነባለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 21. | ከቤተሰቦቼ ጋር በተደጋጋሚ ወደ ቤተመጻሕፍት እሄዳለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 22. | የሚነበቡ ነገሮችን ከጓደኞቼ ጋር መዋዋስ እወዳለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 23. | አንዳንድ ጊዜ ለሌሎች ሰዎች ጽሑፎችን አነብላቸዋለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 24. | ስለማነበው ነገር ለጓደኞቼ መናገር እወዳለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 25. | ጓደኞቼን በትምህርት ቤት በማንበብ ተግባር ለመርዳት እፈልጋለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 26. | በተቻለ መጠን በትምህርት ቤት የተወሰነ የማንበብ ተግባር አከናውናለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 27. | ማንበብ እንዳለብኝ ስለማውቅ አነባለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 28. | ሁልጊዜ የማንበብ ተግባሬን መምህሬ እንደሚፈልጉት አድርጌ አከናውናለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 29. | ለእኔ ማንኛውንም የማንበብ ተግባር መጨረስ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 30. | ሁልጊዜ የማንበብ ተግባሬን በወቅቱ ለመጨረስ እሞክራለሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

# አባሪ አራት፤ የፈተናዎች ውጤት

## 4.1. የቅድመ ፈተና ውጤት

| የሙከራ ቡድን | | | | | | | የቁጥጥር ቡድን | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መ.ኮ | መመሪያ አንድ (5 ነጥብ | መመሪያ ሁለት (10 ነጥብ) | መመሪያ ሶስት (5 ነጥብ) | መመሪያ አራት (10 ነጥብ) | ድምር ውጤት (30 ነጥብ) | መ.ኮ | መመሪያ አንድ (5 ነጥብ | መመሪያ ሁለት (10 ነጥብ) | መመሪያ ሶስት (5 ነጥብ) | መመሪያ አራት (10 ነጥብ) | ድምር ውጤት (30 ነጥብ) | |
| **1** | 3 | 4 | 1 | 5 | 13 | **1** | 3 | 4 | 1 | 10 | 18 | |
| **2** | 3 | 3 | 1 | 0 | 7 | **2** | 3 | 5 | 1 | 0 | 9 | |
| **3** | 2 | 2 | 0 | 5 | 9 | **3** | 3 | 10 | 3 | 10 | 26 | |
| **4** | 3 | 2 | 1 | 5 | 11 | **4** | 1 | 4 | 1 | 0 | 6 | |
| **5** | 3 | 6 | 3 | 5 | 17 | **5** | 5 | 5 | 3 | 10 | 23 | |
| **6** | 3 | 1 | 2 | 10 | 16 | **6** | 1 | 2 | 2 | 0 | 5 | |
| **7** | 3 | 5 | 0 | 10 | 18 | **7** | 1 | 5 | 1 | 0 | 7 | |
| **8** | 2 | 3 | 0 | 10 | 15 | **8** | 2 | 3 | 3 | 5 | 13 | |
| **9** | 4 | 5 | 0 | 10 | 19 | **9** | 2 | 3 | 1 | 0 | 6 | |
| **10** | 3 | 5 | 0 | 5 | 13 | **10** | 3 | 4 | 0 | 5 | 12 | |
| **11** | 5 | 6 | 2 | 10 | 23 | **11** | 2 | 6 | 0 | 10 | 18 | |
| **12** | 4 | 9 | 1 | 10 | 24 | **12** | 3 | 1 | 1 | 0 | 5 | |
| **13** | 4 | 6 | 1 | 10 | 21 | **13** | 4 | 5 | 1 | 10 | 20 | |
| **14** | 2 | 4 | 1 | 10 | 17 | **14** | 3 | 7 | 0 | 10 | 20 | |
| **15** | 2 | 2 | 0 | 0 | 4 | **15** | 0 | 5 | 2 | 0 | 7 | |
| **16** | 2 | 3 | 0 | 5 | 10 | **16** | 1 | 3 | 3 | 0 | 7 | |
| **17** | 5 | 8 | 0 | 10 | 23 | **17** | 2 | 6 | 0 | 10 | 18 | |
| **18** | 4 | 8 | 1 | 5 | 18 | **18** | 2 | 6 | 1 | 0 | 9 | |
| **19** | 2 | 5 | 1 | 10 | 18 | **19** | 4 | 6 | 1 | 10 | 21 | |
| **20** | 4 | 9 | 0 | 10 | 23 | **20** | 4 | 3 | 1 | 10 | 18 | |
| **21** | 4 | 6 | 1 | 0 | 11 | **21** | 3 | 5 | 2 | 0 | 10 | |
| **22** | 4 | 7 | 1 | 5 | 17 | **22** | 3 | 6 | 2 | 5 | 16 | |
| **23** | 4 | 6 | 1 | 5 | 16 | **23** | 1 | 3 | 3 | 10 | 17 | |
| **24** | 3 | 5 | 1 | 0 | 9 | **24** | 1 | 3 | 1 | 5 | 10 | |
| **25** | 5 | 4 | 0 | 0 | 9 | **25** | 5 | 4 | 5 | 10 | 24 | |
| **26** | 3 | 4 | 2 | 0 | 9 | **26** | 1 | 2 | 4 | 0 | 7 | |
| **27** | 3 | 5 | 1 | 8 | 17 | **27** | 3 | 3 | 0 | 5 | 11 | |
| **28** | 4 | 6 | 0 | 0 | 10 | **28** | 1 | 6 | 2 | 0 | 9 | |
| **29** | 3 | 6 | 1 | 10 | 20 | **29** | 1 | 2 | 2 | 10 | 15 | |
| **30** | 4 | 4 | 2 | 10 | 20 | **30** | 2 | 3 | 1 | 5 | 11 | |
| **31** | 1 | 6 | 0 | 5 | 12 | **31** | 1 | 3 | 2 | 10 | 21 | |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **32** | 2 | 3 | 2 | 5 | 12 | **32** | 2 | 3 | 3 | 0 | 8 |
| **33** | 2 | 5 | 0 | 5 | 12 | **33** | 3 | 4 | 3 | 0 | 10 |
| **34** | 3 | 4 | 0 | 0 | 7 | **34** | 0 | 2 | 3 | 10 | 15 |
| **35** | 3 | 6 | 0 | 5 | 14 | **35** | 1 | 0 | 3 | 0 | 4 |
| **36** | 2 | 2 | 5 | 0 | 9 | **36** | 5 | 3 | 0 | 5 | 13 |
| **37** | 1 | 6 | 0 | 0 | 7 | **37** | 0 | 6 | 3 | 0 | 9 |
| **38** | 2 | 5 | 0 | 5 | 12 | **38** | 0 | 1 | 2 | 10 | 13 |
| **39** | 1 | 2 | 0 | 0 | 3 | **39** | 1 | 6 | 0 | 0 | 7 |
| **40** | 1 | 4 | 1 | 5 | 11 | **40** | 2 | 4 | 3 | 5 | 14 |
| **41** | 2 | 1 | 1 | 0 | 4 | **41** | 0 | 2 | 2 | 0 | 4 |
| **42** | 2 | 4 | 2 | 0 | 8 | **42** | 1 | 0 | 4 | 0 | 5 |
| **43** | 3 | 4 | 1 | 0 | 8 | **43** | 3 | 3 | 4 | 0 | 10 |
| **44** | 4 | 5 | 1 | 10 | 20 | **44** | 3 | 4 | 0 | 0 | 7 |
| **45** | 1 | 6 | 0 | 5 | 12 | **45** | 2 | 4 | 0 | 10 | 16 |
| **46** | 2 | 3 | 0 | 0 | 5 | **46** | 2 | 4 | 2 | 5 | 13 |
| **47** | 4 | 7 | 1 | 10 | 22 | **47** | 1 | 3 | 1 | 10 | 15 |
| **48** | 4 | 7 | 2 | 10 | 23 | **48** | 2 | 3 | 2 | 10 | 17 |
| **49** | 4 | 6 | 2 | 10 | 22 | **49** | 1 | 4 | 4 | 0 | 9 |
| **50** | 4 | 2 | 1 | 0 | 7 | **50** | 3 | 1 | 2 | 0 | 6 |
| **51** | 3 | 6 | 1 | 10 | 20 | **51** | 1 | 2 | 2 | 10 | 15 |
| **52** | 4 | 4 | 2 | 10 | 20 | **52** | 2 | 3 | 1 | 5 | 11 |
| **53** | 5 | 6 | 2 | 10 | 23 | **53** | 2 | 6 | 0 | 10 | 18 |
| **54** | 4 | 9 | 1 | 10 | 24 | **54** | 3 | 1 | 1 | 0 | 5 |

## 4.2. የድህረ ፈተና ውጤት

| የሙከራ ቡድን | | | | | | የቁጥጥር ቡድን | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | መመሪያ አንድ (5 ነጥብ | መመሪያ ሁለት (10 ነጥብ) | መመሪያ ሶስት (5 ነጥብ) | መመሪያ አራት (10 ነጥብ) | ድምር ውጤት (30 ነጥብ) | ተ.ቁ | መመሪያ አንድ (5 ነጥብ | መመሪያ ሁለት (10 ነጥብ) | መመሪያ ሶስት (5 ነጥብ) | መመሪያ አራት (10 ነጥብ) | ድምር ውጤት (30 ነጥብ) |
